የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ — የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 27
ADDIS ABABA – 6th March, 1997

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፪/፲፱፺፱ ዓ.ም. የፈጠራ ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... ገጽ ፫፻፺፪

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 12/1997 Inventions, Minor Inventions and Industrial Designs Council of Ministers Regulations ..... Page 392

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፪/፲፱፺፱ የፈጠራ ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፯፯ አንቀጽ ፭ እና የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፫/፲፱፻፹፯ በአንቀጽ ፶፫ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፈጠራ ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፪/፲፱፻፺፱ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩· "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ነው ፤

፪· "መርማሪ" ማለት ለፓተንት ፣ ለግልጋሎት ሞዴል ሰርተፊኬት ወይም ለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ሰርተፊኬት የሚቀርብን ማመልከቻ እንዲመረምር በኮሚሽኑ የተሰየመ ባለሙያ ነው ፤

፫· "ባለ ፓተንት" ማለት የፓተንት ወይም የአስገቢ ፓተንት ባለቤት ነው ፤

፬· "አዋጅ" ማለት የፈጠራ ፣ የአነስተኛ ፈጠራ እና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፫/፲፱፻፹፯ ነው ።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 12/1997 INVENTIONS, MINOR INVENTIONS AND INDUSTRIAL DESIGNS COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 53(1) of the Inventions, Minor Inventions & Industrial Designs, Proclamation No. 123/1995

CHAPTER ONE
General

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as "Inventions, Minor Inventions and Industrial Designs Council of Ministers Regulations No. 12/1997."

2. *Definitions*

In these Regulations, unless the context otherwise requires:

1) "Commission" shall mean the Ethiopian Science and Technology Commission;
2) "Examiner" shall mean a person designated by the Commission to examine an application for a patent, utility model certificate or certificate of registration of an industrial design;
3) "Patentee" shall mean the owner of a patent or a patent of introduction;
4) "Proclamation" shall mean the Proclamation Concerning Inventions, Minor Inventions and Industrial Designs, proclamation No. 123/1995.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 20.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹፻፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· ክፍያዎች

በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ (፪) መሰረት የሚፈጸሙ ክፍያዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ I በተዘረዘረው መሠረት ይሆናል ።

፬· ቅጾች

፩· በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ቅጾች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ II ላይ የተመለከቱት ናቸው ።

፪· ኮሚሽኑ የታተሙ ቅጾችን ቅጅዎች ያለ ክፍያ ያቀርባል ።

፭· ሰነዶች ስለሚቀርቡበት ቋንቋና ትርጉም

፩· ማናቸውም ማመልከቻ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅረብ አለበት።

፪· በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ የማመልከቻ አካል የሆነ ወይም ሌላ ሰነድ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ያልተዘጋጀ ከሆነ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ከዋናው ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት ።

፮· ስለስም ፡ አድራሻ ፡ ዜግነትና የመኖሪያ ቦታ· ጥቆማ

፩· ከኢትዮጵያዊያን በስተቀር የአንድ ተፈጥሮአዊ ሰው ስም የቤተሰብን ስም በማስቀደም በቤተሰብና በመጀመሪያ ስም መገለፅ ያለበት ሲሆን ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካሎች ደግሞ ሙሉ ሕጋዊ መጠሪያ ስማቸው መመልከት ይኖርበታል ።

፪· ማናቸውም አድራሻ አመልካቹ የሚገኝበትን የተሟላ አድራሻ በተለይም የፖስታ ሳጥን ፡ የቴሌግራፍ ፡ የቴሌክስ፡ የስልክ ወይም የፋክስ ቁጥር ሊያመለክት ይገባል ።

፫· ዜግነት አንድ ሰው ዜጋ በሆነበት አገር ስም መገለጽ አለበት ። የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ የተቋቋመ በትን ሀገር ስም የሚገልጽ ሆኖ ዋናው መሥሪያ ቤት የተመዘገበበትን ዝርዝር መግለጫ የያዘ መሆን ይኖር በታል።

፬· የመኖሪያ ቦታ አንድ ሰው የሚኖርበትን ሀገር ስም ጭምር የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል ።

፯· በሽርካዎች ፡ በኩባንያዎችና በማሕበራት ስለሚደረግ ፊርማ

፩· ማናቸውም ሰነድ በሽርካው ወይም በኩባንያው ወይም በማሕበር ስም የሚፈረመው ሥልጣን በተሰጣቸው ሰዎች ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚፈረም ሰነድ ላይ የሽርካው ፡ የኩባንያው ወይም የማሕበሩ ማሕተም ሊያርፍበት ይገባል ።

፰· ስለውክልና

የውክልና ሠነድ ከማመልከቻው ጋር ወይም ከምዝገባው ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ ይችላል ። ውክልናው በአዋጁ አንቀጽ ፱(፯) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፰ በተደነገገው መሠረት ካልተፈጸመ ማመልከቻው ከማስመዝገብ ውጭ በወኪሉ በየደረጃው የተከናወኑ ተግባራት እንዳልተፈፀሙ ይቆጠራሉ ።

ምዕራፍ ሁለት
ፓተንት
ክፍል አንድ
ስለማመልከቻ እና የፓተንት አሰጣጥ ስርዓት

3. *Fees*

The fees to be paid in accordance with Article 53(2) of the proclamation shall be based on schedule I (schedule of fees) annexed to these regulations.

4. *Forms*

1) The forms referred to in these Regulations are those set out in schedule II (schedule of forms) annexed to and forming part of these regulations.
2) Copies of the printed forms shall be furnished free of charge by the Commission.

5. *Language of Documents and Translations*

1) Any Application shall be submitted in the English or Amharic language.
2) Any document forming part of an application or submitted to the Commission pursuant to the Proclamation or these Regulations and which is in a Language other than English or Amharic shall be accompanied by a translation into English or Amharic.

6. *Indication of Name, Address, Nationality and Residence*

1) Names of natural persons except Ethiopians shall be indicated by the person's family name and given name(s), the family name being indicated before the given mame(s), the names of legal entities shall be indicated by their full official designations.
2) Any address shall indicate the full address of the applicant in particular post office box, telegraphic, telex & fax number.
3) Nationality shall be indicated by the name of the state of which a person is a national; legal entities shall indicate the name of the state under whose law they are constituted and full particulars of their registered head office.
4) Residence shall be indicated by the name of the state of which a person is a resident.

7. *Signature by Partnerships, Companies and Associations*

1) A document purporting to be signed for or on behalf of a partnership or a company or an association shall be signed by persons who are authorized to sign the document.
2) A document to be signed in accordance with sub Article (1) of this Article shall have the seal of the partnership; company or association.

8. *Representation*

The power of attorney appointing an agent may be filed together with the application or within two months from its filing date. Where the appointment is not made in accordance with Article 9(7) of the proclamation and Article 48 of these Regulations, any procedural steps taken by the agent other than the filing of the application shall be deemed not to have been taken.

CHAPTER TWO
Patents
Section One
Application and procedure for grant of Patents

፱· ስለፓተንት ምደባ
ከፓተንት አሰጣጥና ሕትመት ጋር ለተዛመዱ ጉዳዮች እንዲሁም የፍለጋ ፋይሎችን ለማኖር ኮሚሽኑ እ·ኤ·አ ማርች ፳፬/፲፱፻፸፩ ዓ·ም በስትራስበርግ ስምምነት የፀደቀውንና በተከታታይ ሕትመቶች የተሻሻለውን ዓለም አቀፍ የፓተንት ምደባ ስርዓት ይጠቀማል ።

፲· የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ
፩· የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ በቅፅ ፩ ተሞልቶ እና በእያንዳንዱ አመልካች ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል ።
፪· ጥያቄው የእያንዳንዱን አመልካች ስም ፣ አድራሻ ፣ ዜግነትና መኖሪያ ማመልከት ይኖርበታል ።
፫· አመልካቹ የፈጠራ ሠራተኛው ሲሆን ጥያቄው ይህንኑ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል ። ሆኖም አመልካቹ የፈጠራ ሰራተኛ ካልሆነ ጥያቄው የእያንዳንዱን የፈጠራ ሰራተኛ ስም እና አድራሻ እንዲሁም አመልካቹ በፓተንቱ ላይ ያለውን መብት የሚያስረዳ መግለጫ መያዝ ይኖርበታል።
፬· አመልካቹ በወኪል ከተወከለ ጥያቄው ይህንኑ ማመል ከትና የወኪሉን ስምና አድራሻ መግለፅ ይኖርበታል ።
፭· የፈጠራው ርዕስ አጠር ያለና ቢቻል ከሁለት እስከ ሰባት ባልበለጡ ቃላት ሊገለጽ የሚችል መሆን ይኖርበታል ።

፲፩· ስለ መግለጫ
፩· መግለጫው በቅድሚያ በመጠይቁ ላይ እንደተመለከተው የፈጠራውን ርዕስ የሚገልጽ ሆኖ ፤
ሀ) ከፈጠራው ጋር ግንኙነት ያለውን የቴክኒክ መስክ የሚያመለክት ፤
ለ) በአመልካቹ እስከታወቀ ድረስ ፈጠራውን ለመረዳት ፣ ለመፈለግ ፣ እና ለመመርመር ጠቃሚ የሆኑ መነሻ ጥበቦችን በይበልጥም እነኝህኑ ጥበቦች የሚያመለክቱ ሰነዶችን የሚጠቁም ፤
ሐ) ፈጠራው ያሚላል ተብሎ የታለመውን ተግባር የሚገልጽ ፤
መ) በሙያው የሰለጠነ ሰው ፈጠራውን ተግባራዊ ሊያደርገው በሚችልበት አኳኋን በበቂና በተሟላ ሁኔታ የሚያብራራ እና ጠቃሚ ውጤት ካለው ከመነሻ ጥበቡ ጋር በማነፃፀር የሚገልጽ ፤
ሠ) ከቀደምት ጥበብ ጋር ሲወዳደር ፈጠራው የሚኖረውን በጎ ጎን ወይም ውጤታማነት የሚገልጽ ፤
ረ) ሥዕሎች ካሉ በሥዕሎቹ ውስጥ ያሉ ቁጥሮችን በአጭሩ የሚዘረዝር ፤
ሰ) ፈጠራውን በሥራ ላይ ለማዋል በአመልካቹ ከተተለሙ መንገዶች ቢያንስ አንዱን የሚገልጽና እንደ አስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመጠቀም እና ስዕሎች ካሉ ከሥዕሎች ጋር በማገናዘብ የሚያቀርብ ፤
ሸ) ከፈጠራው መግለጫ ወይም ባህርይ ግልፅ ሊሆን ካልቻለ ፈጠራው በኢንዱስትሪ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን እና ፈጠራው የሚሰራበትንና ግልጋሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ ወይም አገልግሎት መስጠት ብቻ ከሆነም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል ።

9. *Classification of Patents*
The Commission shall apply the International Patent Classification, as adopted under the Strasbourg Agreement of March 24,' 1971 and updated in its subsequent editions, for all purposes relating to the grant and publication of patents, as well as for the maintenance of classified search files.

10. *Request for Grant of Patent*
1) The request for the grant of a patent shall be made on Form No. 1 and shall be signed by each applicant.
2) The request shall indicate each applicant's name, address, nationality and residence.
3) Where the applicant is the inventor, the request shall contain a statement to that effect, and, where he is not, it shall indicate each inventor's name and address and be accompanied by a statement justifying the applicant's right to the patent.
4) If the applicant is represented by an agent, the request shall so indicate and state the agent's name and address.
5) The title of the invention shall be short, preferably from two to seven words, and precise.

11. *Description*
1) The description shall first state the title of the invention as appearing in the request and shall:
(a) specify the technical field to which the invention relates;
(b) indicate the background art which, as far as known to the applicant, can be regarded as useful for the understanding, searching and examination of the invention, and preferably cite documents reflecting such art;
(c) specify the task which the invention is designed to fulfil;
(d) disclose the invention in a manner sufficiently clear and complete so as to enable a person having ordinary skill in the art to carry it out, and state its advantageous effects, if any, with reference to the background art;
(e) state the merits or effective results of the invention as compared with the prior art;
(f) briefly describe the figures in the drawings, if any;
(g) set forth at least one mode contemplated by the applicant for carrying out the invention; this shall be done in terms of examples, where appropriate, and with reference to the drawings, if any;
(h) indicate explicitly, when it is not obvious from the description or nature of the invention, the way in which the invention is industrially applicable and in which it can be made and used, or, if it can only be used, the way in which it can be used.

፪· በፈጠራው ባህሪ ምክንያት ፈጠራውን በተለየ መንገድ ወይም ቅደም ተከተል መግለጹ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳትና በአጭሩ ለማቅረብ የሚያመች ሆኖ ካልተገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በተመለከተው መንገድ እና ቅደም ተከተል መግለጫው መቅረብ ይኖርበታል ።

፫· የፈጠራው መግለጫ የኬሚካል ወይም የሂሳብ ፎርሙላ ዎችን እንጅ የንግድ ማስታወቂያዎችን ሊይዝ አይችልም።

፬· መግለጫው ፈጠራውን የበለጠ ለማብራራት የሚረዱ ነገሮችን ብቻ መያዝ የሚችል ሆኖ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያላገኘ አዲስ ቃል ወይም ሙያ ነክ ቃልን የያዘ እንደሆነ ቃሉ መገለጽ ይኖርበታል ።

፲፪· ስለመብት ወሰን ጥያቄ

፩· የመብት ወሰን ጥያቄ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚፈለግን ጉዳይ በፈጠራው ቴክኒካዊ ገፅታዎች አማካኝነት ግልጽ በሆነና አጠር ባለ መንገድ የሚገልጽና አንድን ምርት ወይም የምርት ሒደት የሚመለከት ይሆናል ።

፪· የመብት ወሰን ጥያቄዎች ብዛት የፈጠራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት አግባብነት ያለው ሊሆን ይገባል ። ብዙ የመብት ወሰን ጥያቄዎች በሚኖሩበት ጊዜ ተከታታይ የአረብኛ ቁጥር ይሰጣቸዋል ።

፫· በመብት ወሰን ጥያቄ ላይ የሚገለጽ የቴክኒክ ቃል በመግለጫው ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት ። የመብት ወሰን ጥያቄዎች የኬሚካል ወይም የሂሳብ ፎርሙላዎችን እንጂ ሥዕሎችን አይዙም ።

፬· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመብት ወሰን ጥያቄ ፣

ሀ) ፈጠራውን ለመግለጽ አስፈላጊና በጣምራ የቀደምት ጥበብ አካል የሆኑትን የፈጠራውን ቴክኒካዊ ባህርያት የሚያመለክት መግለጫ ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬)(ሀ) ከተመለከቱት ባህርያት ጋር በመጣመር ጥበቃ ሊደረግለት የተፈለገውን ቴክኒካዊ ባህርይ በአጭሩ የሚገልጽ "የሚገለጸው" "የሚለየው" "ማሻሻያው የሚያካትተው" በሚሉ ሐረጐች የሚጀምር የመለያ ባህርይ ክፍል ሊይዝ ይገባል ።

፭· የግድ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር የመብት ወሰን ጥያቄ የፈጠራውን ቴክኒካዊ ባህርያት አስመልክቶ መግለጫ ዎችን ወይም ስዕሎችን መሠረት ያደረጉ በተለይም "በመግለጫው ——— ክፍል እንደተገለጸው" ፣ ወይም "በስዕሉ ——— ላይ እንደተመለከተው" በሚሉ ተጠቃሾች ላይ አይወሰኑም ።

፮· ማመልከቻው ሥዕሎችን ያካተተ እንደሆነ በመብት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የተገለጹት ቴክኒካዊ ባህርያት ጠቋሚ ምልክቶችን ቢያስከትሉና ምልክቶቹም በጥቅም ላይ በዋሉ ጊዜ በቅንፍ ውስጥ ቢቀመጡ ይመረጣል ። ጠቋሚ ምልክቶቹ የመብት ወሰን ጥያቄውን በፍጥነት ለመገንዘብ የሚያገለግሉ ካልሆኑ መካተት የለባቸውም ።

፯· ከማመልከቻው የምዝገባ ቀን በኋላ የቀረበ በቀድሞ ማመልከቻ ውስጥ ከሚገኙት የመብት ወሰን ጥያቄዎች ጋር ያልተዛመደ የመብት ወሰን ጥያቄ በአመልካቹ ምርጫ እንደተሻሻለ ወይም እንደ አዲስ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ።

2) The manner and order specified in sub-Article (1) of this Article shall be followed except when, because of the nature of the invention, a different manner or a different order would result in a better understanding and a more concise presentation.

3) The description of the invention may contain chemical or mathematical formulae but no commercial advertising.

4) The description may only contain material which will contribute to the elaboration of the invention and if a newly joined word or a professional word which has not generally been accepted must be used, it shall be explained.

12. *Claims*

1) The claim shall define clearly and concisely the matter for which protection is sought in terms of the technical features of the invention and shall pertain to either product or process.

2) The number of the claims shall be reasonable taking into account the nature of the invention; where there are several claims, they shall be numbered consecutively in arabic numerals.

3) The technical terminology used in the claims shall be consistent with that used in the description. The claims may contain chemical or mathematical formulae but not drawings.

4) Whenever appropriate a claim shall contain:
   (a) a statement indicating those technical features of the invention which are necessary for the definition of the latter but which, in combination, are part of the prior art,
   (b) a characterizing portion--preceded by the words "characterized in that," "characterized by," "wherein the improvement comprises," or any other words to the same effect--stating concisely the technical feature which, in combination with the features stated under sub-Article 4(a) of this Article, is desired to be protected.

5) A claim shall not, except where absolutely necessary, rely in respect of the technical features of the invention on references to the description or drawings; in particular, it shall not rely on such references as "as described in part... of the description," or "as illustrated in figure... of the drawings."

6) Where the application contains drawings, the technical features mentioned in a claim shall preferably be followed by the reference signs relating to such features; when used, the reference signs shall preferably be placed between parentheses; if inclusion of reference signs does not particularly facilitate quicker understanding of a claim, it should not be made.

7) Any claim submitted after the filing date of the application and which is not identified with the claims previously appearing in the application shall, at the choice of the applicant, be submitted either as an amended claim or as a new claim.

፰· በቀድሞ ማመልከቻ ላይ ሰፍሮ የነበረ ማናቸውም የመብት ወሰን ጥያቄ የተሰረዘ እንደሆነ የቀድሞውን የመብት ጥያቄ የመለያ ቁጥሩን በመጥቀስ "ተሠርዟል" የሚል ቃል ይደረግበታል ።

፲፫· ሥዕሎች

፩· ለፓተንት የቀረበ ማመልከቻ አካል የሆኑ ሥዕሎች የሚቀርቡበት ወረቀት ጥቅም ላይ የሚውለው ክፍል ስፋት ከ፳፮·፪ ሣ·ሜ በ፲፯ ሣ·ሜ መብለጥ የለበትም ። በእነኝህ ወረቀቶች በጥቅም ላይ በሚውለው ወይም በዋለው ቦታ ዙሪያ ክፈፍ ሊኖር አይገባም ። የአነስተኛ ህዳጎች መጠን ፣

ከላይ	፪ ነጥብ ፭ ሣ·ሜ
ከግራ ጎን	፪ ነጥብ ፭ ሣ·ሜ
ከቀኝ ጎን	፩ ነጥብ ፭ ሣ·ሜ
ከታች	፩ ነጥብ ዜሮ ሣ·ሜ ይሆናል ።

፪· ሥዕሎች ፣

ሀ) አጥጋቢ የሆነ ቅጅ ለማውጣት እንዲቻል ቀለም አልባ በሆኑ በበቂ መጠን ደማቅና ጥቁር እንዲሁም ወጥ ስፋትና ግልፅነት ባላቸው መስመሮችና ጭረቶች ሊሰሩ ይገባል ፣

ለ) የአንድ ሥዕል ክፍል እይታ የመሪ መስመሮችንና የአመልካች ምልክቶችን ተነባቢነት በማይከለክል አኳኋን ተጋዳሚና ተደጋጋሚ መስመሮችን በመጠቀም መታየት ይኖርበታል ፣

ሐ) የሥዕሎች ስኬልና የግራፊክ አሰፋፈራቸው የግል ጽነት ደረጃ ወደ ሁለት ሶስተኛ በተቀነሰ የፎቶ ግራፍ ቅጅአቸው ሁሉንም ዝርዝር ያለምንም ችግር በቀላሉ ለመለየት የሚረዳ መሆን አለበት ፣ በተለየ ምክንያት ስኬሉ በሥዕሉ ላይ ተሰጥቶ ከሆነ በግራፍ መልክ መቀመጥ ይኖርበታል ፣

መ) በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ቁጥሮች ፣ ፊደላት እና ጠቋሚ ምልክቶች ቀላልና ግልጽ መሆን ያለባቸው ሲሆን ቅንፎች ፣ ክቦች እና የጥቅስ ምልክቶች ከቁጥሮች እና ከፊደላት ጋር በተያያዘ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤

ሠ) ለሥዕሉ ጥራት ሲባል የመጠን ልዩነት ማድረግ አስፈላጊ እስካልሆነ ድረስ የአንድ ሥዕል አካሎች መጠን እርስ በእርሳቸው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው ፣

ረ) የቁጥሮችና የፊደላት ከፍታ ከዜሮ ነጥብ ፴፪ ሣ·ሜ ማነስ የሌለበት ሲሆን ሥዕሎችን ለማመልከት የላቲን እና የተለመደም ሆኖ ሲገኝ የግሪክ ፊደላትን መጠቀም ይቻላል ፣

ሰ) አንድ የሥዕል ወረቀት ብዙ ምስሎችን ሊይዝ ይችላል። ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወረቀቶች ላይ የተሣሉ ሥዕሎች አንድ ሙሉ ሥዕልን የሚመሠርቱ ከሆነ እነኝሁ ሥዕሎች የስእሉን ማናቸውም አካል ሳይደብቁ ሊቀናጁ በሚችሉበት መንገድ መዘጋጀት አለባቸው ። የተለያዩት ሥዕሎች በግልጽ አንዱ ከሌላው የሚለዩ ሆነው ቦታ ሳይባክን ሊቀናጁ የሚችሉ መሆን አለባቸው ፣ ለየገፁ ከተሰጠው ቁጥር ጋር ሳይገናዘቡ ለተለያዩ ሥዕሎች ተከታታይነት ያለው የአረብ ቁጥር መሰጠት ይኖርበታል ፣

8) The deletion of any claim previously appearing in the application shall be made by indicating the number of the previous claim followed by the word "canceled".

13. *Drawings*

1) Drawings forming part of an application for a patent shall be on sheets, the usable surface area of which shall not exceed 26.2 cm by 17 cm. The sheets shall not contain frames round the usable or used surface. The minimum margins shall be as follows:

top	2.5 cm
left side	2.5 cm
right side	1.5 cm
bottom	1.0 cm

2) Drawings shall be executed as follows:

(a) without colouring in durable, black, sufficiently dense and dark, uniformly thick and well-defined lines and strokes to permit satisfactory reproduction;

(b) cross sections shall be indicated by hatching which does not impede the clear reading of the reference signs and leading lines;

(c) the scale of the drawings and the distinctness of their graphical execution shall be such that a photographic reproduction with a linear reduction in size to two thirds would enable all details to be distinguished without difficulty. If, as an exception, the scale is given on a drawing it shall be represented graphically;

(d) all numbers, letters and reference signs appearing in the drawings shall be simple and clear and brackets, circles and inverted commas shall not be used in association with mumbers and letters;

(e) elements of the same figure shall be in proportion to each other, unless a difference in proportion is indispensable for the clarity of the figure;

(f) the height of the numbers and letters shall not be less than 0.32 cm and for the lettering of drawings, the Latin and, where customary, the Greek alphabets shall be used;

(g) the same sheet of drawings may contain several figures. Where figures drawn on two or more sheets are intended to form one whole figure, the figures on the several sheets shall be so arranged that the whole figure can be assembled without concealing any part of the partial figures. The different figures shall be arranged without wasting space, clearly separated from one another. The different figures shall be numbered consecutively in arabic numerals, independently of the numbering of the sheets;

ሸ) በመግለጫ ወይም በመብት ወሰን ጥያቄዎች ላይ ያልተገለጹ ጠቋሚ ምልክቶች በስዕሎች ላይ ወይም በሥዕሎች ላይ ያልተገለጹ ጠቋሚ ምልክቶች በመግለጫው ወይም በመብት ወሰን ጥያቄዎች ላይ መታየት የለባቸውም ። አንድ ዓይነት ገጽታዎች በጠቋሚ ምልክቶች ከተገለጹ ይህ ሁኔታ በማመልከቻው ውስጥ ያለምንም ለውጥ ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል ፤

ቀ) ስዕሎችን ለመረዳት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ማብራሪያ ጽሑፍ ተያይዞ መቅረብ የለበትም። እንደ "ውሀ" "እንፋሎት" "ክፍት ነው" "ዝግ ነው" በክፍል ሀሀ" ያለ ቃል ወይም ቃላት እንዲሁም በብሎክ ስኬማቲክ ወይም በፍሎው ሺት ዲያግራም ውስጥ አጭርና ገላጭ ቃላት መካተት አይኖርባቸውም ፤

በ) ስዕሎች ያረፉባቸው ገጾች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮(፯) በተደነገገው መሠረት ቁጥር ሊሰጣቸው ይገባል ።

፫) የፍሎው ሺት እና ዲያግራሞች ሥዕሎች ተደርገው ይወሰዳሉ ።

፲፬· <u>የፈጠራ አጭር ይዘት</u>

፩· የፈጠራው አጭር ይዘት በአንድ የተወሰነ ጥበብ ዘርፍ ቀልጣፋ ፍለጋ ለማድረግ የሚያገለግል መሳሪያ በመሆን መዘጋጀት ያለበት ሆኖ ተጠቃሚው ሙሉ ማመልከቻውን ለመመልከት አስፈላጊ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችለው ሆኖ መዘጋጀት አለበት ።

፪· የፈጠራው አጭር ይዘት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

ሀ) ከፈጠራው ጋር የሚዛመደውን የቴክኒክ መስክ የሚጠቁም እና ቴክኒካዊ ችግሩን ፣ ፈጠራው ለችግሩ የሚሰጠውን ዋና መፍትሄ እና የፈጠራውን ዋና ጥቅም ወይም ጥቅሞች በግልጽ ለመረዳት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ በመግለጫው በመብት ወሰን ጥያቄውና በስዕሎች የተካተቱ የፈጠራው ገሀድነት ማጠቃለያ፤

ለ) እንደአግባቡ በማመልከቻው ውስጥ ከተካተቱ የኬሚካል ፎርሙላዎች መካከል በተሻለ ሁኔታ ፈጠራውን የሚገልጽ የኬሚካል ፎርሙላ።

፫· የፈጠራው ገሀድነት በሚፈቅደው መጠን የፈጠራው አጭር ይዘት አጠር ያለ ሆኖ በፈጠራው ይገኛል ተብሎ ስለሚጠበቅ በጎ ጎን ወይም ዋጋ ወይም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ስለሚባልበት ሁኔታ መግለጫ መያዝ የለበትም ።

፬· በፈጠራው አጭር ይዘት የተገለፀና በማመልከቻው ውስጥ ባሉ ስዕሎች የተመለከተ እያንዳንዱ አብይ ቴክኒካዊ ባህርይ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡ ጠቋሚ ምልክቶችን ማስከተል አለበት ።

፭· የፈጠራው አጭር ይዘት በአመልካቹ ከቀረቡት ሥዕሎች መካከል በይበልጥ ገላጭ ከሆነው ሥዕል ጋር አብሮ መሆን አለበት ።

፲፭· <u>መለኪያዎች ፣ ቃላቶች እና ምልክቶች</u>

፩· የክብደት እና የርዝመት መለኪያዎች በሜትሪክ ሲስተም መገለጽ አለባቸው ።

፪· የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴንትግሬድ መገለጽ አለበት ።

፫· እፍጋት በሜትሪክ አሀድ መገለፅ ይኖርበታል ።

(h) reference signs not mentioned in the description or claims shall not appear in the drawings, and vice versa. The same features, when denoted by reference signs, shall, through out the application, be denoted by the same signs;

(i) the drawings shall not contain textual matter, except, when required for the understanding of the drawings, a single word or words such as "water", "steam", "open", "closed", "section on AA" and in the case of electric circuits and block schematic or flow sheet diagrams, a few short catch words;

(j) the sheets of the drawings shall be numbered in accordance with Article 16(7) of these regulations.

3) Flow sheets and diagrams are considered as drawings.

14. *Abstract*

1) The abstract shall be so drafted that it can efficiently serve as a scanning tool for purposes of searching in the particular art thereby assisting the user in formulating an opinion on whether there is a need for consulting the application itself.

2) The abstract shall contain:

(a) a summary of the disclosure as contained in the description, the claims, and any drawings, indicating the technical field to which the invention pertains and drafted in a way which allows the clear understanding of the technical problem, the gist of the solution of that problem through the invention, and the principal use or uses of the invention;

(b) where applicable, the chemical formula which, among all the formula contained in the application, best characterizes the invention.

3) The abstract must be as concise as the disclosure permits and shall not contain statements on the alleged merits or value of the claimed invention or in its speculative application.

4) Each main technical feature mentioned in the abstract and illustrated by a drawing in the application shall be followed by a reference sign, placed between parentheses.

5) The abstract shall be accompanied by the most illustrative of any drawings furnished by the applicant.

15. *Measures, Terminology and Signs*

1) Units of weights and mesures shall be expressed in terms of the metric system.

2) Temperature shall be expressed in degree centigrade.

3) Density shall be expressed in metric units.

፬· ሙቀት ፣ ኃይል ፣ ብርሀን ፣ ድምፅ እና መግነጢሳዊነት እንዲሁም የሂሳብ ፎርሙላዎችን እና የኤሌክትሪክ አሀዶችን ለማመልከት በጥቅም ላይ ያሉ አጠቃላይ ደንቦችን መከተል ያስፈልጋል ። ለኬሚካል ፎርሙላዎች በአጠቃላይ አገልግሎት ላይ የዋሉ ምልክቶችን የአቶም ክብደቶችን እና የሞሉኪዊል ፎርሙላዎችን መገልገል ያስፈልጋል ።

፭· በአንድ የጥበብ መስክ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙት የቴክኒክ ቃላትና ምልክቶች ብቻ በጥቅም ላይ መዋል አለባቸው ።

፮· በማመልከቻ ውስጥ የቃላትና ምልክቶች አጠቃቀም መዛባት የለበትም ።

፲፮· <u>የቅጅዎች ብዛትና የአቀራረብ መልክ</u>

፩· የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩(፯) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማመልከቻዎችና ማናቸውም ተያይዘው የሚቀርቡ ማብራሪያዎች ወይም ሠነዶች በሦስት ቅጅ መቅረብ አለባቸው ። ነገር ግን ኮሚሽኑ አመልካቹን ተጨማሪ ቅጂዎች እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል ።

፪· ሁሉም የማመልከቻው ክፍሎች በፎቶግራፍ ፣ በኤሌክትሮ ስታቲክ ሂደት ፣ በፎቶ አፍ ሴትና በማይክሮ ፊልም በቀጥታ ሊባዙ በሚችሉበት መልክ መቅረብ አለባቸው ።

፫· በማመልከቻው ውስጥ ያለ የእያንዳንዱ ወረቀት አንዱ ገጽ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ።

፬· ሁሉም የማመልከቻው ክፍሎች ተጣጣፊ ፣ ጠንካራ ፣ ነጭ፣ ለስላሳ ፣ የማያንፀባርቅ እና ረጅም እድሜ በሚቆይ ወረቀት ላይ ሠፍረው መቅረብ አለባቸው ።

፭· የወረቀቶች መጠን ኤ፬ (፳፱ ነጥብ ፯ ሣ·ሜ × ፳፩ ሣ·ሜ) መሆን አለበት።

፮· የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫(፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረቀቶቹ አነስተኛ ህዳጎች እንደሚከተለው መሆን አለባቸው ።

ሀ) ከመጀመሪያው ገፅ በስተቀር የሌሎቹ ገፆች በሙሉ የላይኛው ህዳግ ፳ ሚ·ማ

ለ) የመጀመሪያው ገፅ የላይኛው ህዳግ ፴ ሚ·ሜ·

ሐ) ወረቀቱ በሚጠረዝበት በኩል ያለው የጎን ህዳግ ፳፭ ሚ·ሜ·

መ) ሌላኛው የጎን ህዳግ ፳ ሚ·ሜ·

ሠ) የታችኛው ህዳግ ፳ ሚ·ሜ·

፯· ሀ) የዓረባዊ ቁጥሮች በሁሉም ወረቀቶች አናት መሀከሉ ላይ በተከታታይ መፃፍ አለባቸው ።

ለ) ለወረቀቶች ተከታታይ ቁጥር ሲሰጥ የማመልከቻው ክፍሎች ጥያቄ ፣ መግለጫ ፣ የመብት ወሰን ፣ አጭር መግለጫ እና ሥዕል በተራ ሊቀመጡ ይገባል ።

ሐ) ለወረቀቶቹ ተከታታይነት ያለው ቁጥር አሰጣጥ ሶስት የተለያዩ የቁጥር አሰጣጥ ተራዎችን በመጠቀም ሆኖ የመጀመሪያው ተራ ለጥያቄው ብቻ የሚያገለግልና ከጥያቄው የመጀመሪያው ገፅ የሚጀምር ነው ። ሁለተኛው ተራ ከመግለጫው የመጀመሪያ ገፅ የሚጀምርና የጥበቃ ወሰንን አካትቶ እስከ አጭር ይዘቱ የመጨረሻ ገፅ የሚቀጥል ነው ። ሦስተኛው ተራ ሥዕሎችን ለያዙ ገፆች ብቻ የሚያገለግልና ከስዕሎች የመጀመሪያ ገፅ የሚጀምር ነው ።

4) For indications of heat, energy, light, sound and magnetism, as well as for mathematical formulae and electrical units, rules in general use shall be observed; for chemical formulae, the symbols, atomic weights and molecular formulae, in general use, shall be employed.

5) In general, only such technical terms, signs and symbols shall be used as are generally accepted in the art.

6) The terminology and the signs shall be consistent throughout the application.

16. *Number of Copies and Physical Requirements*

1) Subject to Article 21(7) of these Regulations, the application and any accompanying statements or documents shall be filed in three copies, but the Commission may require the applicant to supply additional copies.

2) All elements of the application shall be so presented as to enable direct reproduction by photography, electrostatic processes, photo-offset and micro filming.

3) Only one side of each sheet contained in the application shall be used.

4) All elements of the application shall be on paper which is flexible, strong, white, smooth, non-shiny and durable.

5) The size of the sheets shall be A4(29.7cm×21 cm).

6) Subject to Article 13(1) of these regulations, the minimum margins of sheets shall be as follows:

(a) upper margin of each page, except the first page: 20mm

(b) upper margin of the first page: 30mm

(c) side margin adjacent to the binding: 25mm

(d) other side margin: 20mm

(e) bottom margin : 20mm

7) (a) All sheets shall be numbered at the top of the sheet, in the middle, in consecutive arabic numerals.

(b) In effecting the sequential numbering of the sheets, the elements of the application shall be placed in the following order: the request, the description, the claims, the abstract, the drawings.

(c) The sequential numbering of the sheets shall be effected by using three separate series of numbering, the first series applying to the request only and commencing with the first sheet of the request, the second series commencing with the first sheet of description and continuing through the claims until the last sheet of the abstract, and the third series being applicable to the sheets of the drawings only and commencing with the first sheet of the drawings.

፫· የማመልከቻው ጽሑፍ መተየብ ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግራፊክ ምልክቶች የኬሚካል ወይም የሂሣብ ፎርሙላዎች እና የተወሰኑ ካራክተሮች በእጅ ሊፃፉ ወይም ሊሣሉ ይችላሉ ።

፬· ሥዕሎች ሲሣሉ ያለ ቀለም ዘላቂነት ባለው ጥቁር በበቂ መጠን ወፈር እና ደመቅ ባሉ አንድ ወጥ ስፋት እና በግልጽ በተቀመጡ መስመሮችና ጭረቶች መሆን አለበት ።

፲፯· <u>የፈጠራ አሀዳዊነት</u>

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፱ (፪) ከሚከተሉት ሦስት አማራጮች በተለይ

ሀ) ለአንድ ምርት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ በተለይ የተጠቀሰውን ምርት ለማምረት የሚረዳ የምርት ሂደት ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ እንዲሁም የተጠቀሰውን ምርት የመጠቀም ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን ፤ ወይም

ለ) ለአንድ የምርት ሂደት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ ለተዘጋጀ መሣሪያ ወይም ዘዴ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን ፤ ወይም

ሐ) ለአንድ ምርት ከሚቀርብ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በተጨማሪ በተለይ የተጠቀሰውን ምርት ለማምረት የሚረዳ የምርት ሂደት ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ እና ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ ለማከናወን በተለይ ለተዘጋጀ መሣሪያ ወይም ዘዴ ራሱን የቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ማካተትን የሚፈቅድ ሆኖ ሊተረጐም ይገባል ።

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፱(፪) አንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ በአንድ መደብ የሚፈረጁ ሆኖም በቀጥታ በአንድ አጠቃላይ የመብት ወሰን የማይካተቱ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ራሳቸውን የቻሉ የመብት ወሰን ጥያቄዎችን ማቅረብ ይፈቀዳል ።

፫· የአዋጁ አንቀጽ ፱(፪) እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ራሱን በቻለ የመብት ወሰን ጥያቄ ስር የተመለከቱት የተለያዩ የፈጠራውን መስኮች የሚመለከቱ ተገቢ ቁጥር ያላቸው ጥገኛ የመብት ወሰን ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል ።

፬· በአዋጁ አንቀጽ ፱(፪) መሠረት የፈጠራ አሀዳዊነት መመዘኛ ለማያሟላ ማመልከቻ ፓተንት መስጠት ለፓተንቱ መሰረዝ ምክንያት አይሆንም ።

፲፰· <u>ማመልከቻን ስለማሻሻልና መከፋፈል</u>

፩· ማሻሻያው በመጀመሪያው ማመልከቻ ከተገለፀው ውጪ የሆነ ነገር የማያስከትል ከሆነ አመልካቹ ፓተንት እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ማመልከቻውን ማሻሻል ይችላል ።

፪· እያንዳንዱ ክፋይ ማመልከቻ በመጀመሪያው ማመልከቻ ላይ ከተገለጸው ውጪ የሆነ ነገር የማያስከትል ከሆነ ፓተንት እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ አመልካቹ ማመልከቻውን ወደ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ማመልከቻዎች ሊከፋፍል ይችላል ።

8) The text matter of the application shall be typed; graphic sympols, chemical or mathematical formulae and certain characters, if necessary, may be handwritten or drawn.

9) Drawings shall be executed in durable, black, sufficiently dense and dark, uniformly thick and well defined lines and strokes without colorings.

17. *Unity of Invention*

1) Article 9 (2) of the proclamation shall be construed as permitting, in particular, one of the following three possibilities:

(a) in addition to an independent claim for a given product, the inclusion in the same application of an independent claim for a process specially adapted for the manufacture of the said product, and the inclusion in the same application of an independent claim for a use of the said product; or

(b) in addition to an independent claim for a given process, the inclusion in the same application of an independent claim for an apparatus or means specifically designed for carrying out the said process, or

(c) in addition to an independent claim for a given product, the inclusion in the same application of an independent claim for a process specially adapted for the manufacture of the product, and the inclusion in the same application of an independent claim for an apparatus or means specifically designed for carrying out the process.

2) Subject to Article 9(2) of the proclamation, it shall be permitted to include in the same application two or more independent claims of the same category which cannot readily be covered by a single generic claim.

3) Subject to Article 9(2) of the proclamation, it shall be permitted to include in the same application a reasonable number of dependent claims, claiming specific forms of the invention claimed in an independent claim.

4) The fact that a patent has been granted on an application that did not comply with the requirement of unity of invention under Article 9 (2) of the proclamation shall not be a ground for the invalidation of the patent.

18. *Amendment and Division of Application*

1) The applicant may, up to the time when the application is in order for grant, amend the application, provided that the amendment shall not go beyond the disclosure in the initial application.

2) The applicant may, up to the time when the application is in order for grant, divide the application into two or more applications, provided that each divisional application shall not go beyond the disclosure in the initial application.

፫. እያንዳንዱ ክፋይ ማመልከቻ የመጀመሪያው ማመልከቻ የምዝገባ ቀንና እንደአግባቡ የመጀመሪያው ማመልከቻ የቀዳሚነት ቀን ይኖረዋል ።

፬. አንድ ክፋይ ማመልከቻ የመጀመሪያውን ማመልከቻ የሚጠቅስ ክፍል መያዝ አለበት ።

፭. አመልካቹ ክፋይ ማመልከቻው የመጀመሪያው ማመልከቻ ማናቸውም የቀዳሚነት ጥያቄ ተጠቃሚ እንዲሆን ከፈለገ ክፋይ ማመልከቻው ይህንኑ የሚያመለክት ጥያቄ መያዝ አለበት ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የመጀመሪያው ማመልከቻ የቀዳሚነት መግለጫ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ መሠረት የቀረቡ ሠነዶች ለክፋይ ማመልከቻው የሚያገለግሉ ተደርገው ይወሰዳሉ ።

፮. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቀድመው የገቡ ማመልከቻዎች ቀዳሚነት ለመጀመሪያው ማመልከቻ የተጠየቀ እንደሆነ ክፋይ ማመልከቻው ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው አግባብ ካለው /ካላቸው የቀዳሚነት ጥያቄ/ ጥያቄዎች ነው ።

፲፱. <u>አስቀድሞ ለህዝብ የተገለጸ ፈጠራ እንደቀደምት ጥበብ ስለማይቆጠርበት ሁኔታ</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፫(፫) መሠረት ቀደም ሲል የተከናወነ ፈጠራውን ገሀድ የማድረግ ተግባር እንደቀደምት ጥበብ እንዳይቆጠር ፍላጎት ያለው አመልካች ይህንኑ በማመልከቻው ላይ መግለጽ እና ከማመልከቻው ጋር ወይም ማመልከቻው በገባ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ የገሀድነቱን ሙሉ መግለጫ ማቅረብ አለበት ። ለገሀድነት የበቃው በኢግዚቢሽን ላይ ከሆነ አመልካቹ ከላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የኢግዚቢሽኑ ኃላፊ በሆነው አካል የተዘጋጀና የተፈረመ የኢግዚቢሽኑን ልዩ ባህርይ የሚገልጽና በእር ግጥም ፈጠራው በኢግዚቢሽኑ መቅረቡን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለበት ።

፳. <u>ቀዳሚነትን ስለማሳወቅና ስለቀዳሚ ማመልከቻ ትርጉም</u>

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፲፩(፪) የተገለጸው መግለጫ የሚከተሉትን ማመልከት አለበት፤

ሀ) የቀዳሚውን ማመልከቻ ቀን ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀዳሚውን ማመልከቻ ቁጥር፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ ማመልከቻው የተመደበበትን የዓለም አቀፍ ፓተንት ምደባ መለያ ፤

መ) ቀዳሚ ማመልከቻው ቀርቦበት የነበረው ሀገር ወይም ቀዳሚ ማመልከቻው አህጉራዊ ወይም ዓለምአቀፋዊ ማመልከቻ ከሆነ በማመልከቻው የተመለከቱትን ሀገሮች ፤

ሠ) ቀዳሚ ማመልከቻው አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ከሆነ ማመልከቻው የቀረበበት ጽሕፈት ቤት ።

፪. በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፪) መሠረት የተገለጸው መግለጫ በሚቀርብበት ወቅት የቀዳሚ ማመልከቻው ቁጥር የማይታወቅ ከሆነ መግለጫውን የያዘው ማመልከቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ ባሉ ሶስት ወራት ውስጥ ቁጥሩ መገለጽ አለበት ።

3) Each divisional application shall be entitled to the filing date and, where applicable, the priority date of the initial application.

4) A divisional application shall contain a reference to the initial application.

5) If the applicant wishes a divisional application to benefit from any priority claimed for the initial application, the divisional application must contain a request to that effect; in such a case, the declaration of priority and the documents furnished in accordance with Article 20 of these Regulations for the initial application shall be deemed to relate also to the divisional application.

6) Where the Priorities of two or more earlier applications were claimed for the initial application, a divisional application may benefit only from the priority or priorities that are applicable to it.

19. *Disclosures to be Disregarded for Prior Art Purposes*

An applicant who wishes a disclosure of the invention to be disregarded, in accordance with Article 3 (3) of the proclamation, for prior art purposes, shall so indicate on the application, and shall furnish, in writing, with the application, or within one month of filing the application, full particulars of the disclosure; where the disclosure was made at an exhibition, the applicant shall file, within the same period, a duly authenticated certificate issued by the authority responsible for the exhibition containing particulars of the exhibition and stating that the invention was in fact exhibited there.

20. *Declaration of Priority & Translation of Earlier Application*

1) The declaration referred to in Article 11 (2) of the proclamation shall indicate:
   (a) the date of the earlier application;
   (b) the number of the earlier application, subject to sub-Article (2) of this Article;
   (c) the symbol of the International Patent Classification which has been allocated to the earlier application, subject to sub-Article (3) of this Article;
   (d) the state in which the earlier application was filed or, where the earlier application is a regional or an international application, the states for which it was filed;
   (e) Where the earlier application is a regional or an international application, the office with which it was filed,

2) Where at the time of filing the declaration referred to in Article 11 (2) of the proclamation the number of the earlier application is not known, that number shall be furnished within three months from the date on which the application containing the declaration was filed.

፫· ቀዳሚ ማመልከቻው የዓለም አቀፍ የፓተንት ምደባ መለያ ያልተሰጠው ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተገለጸው መግለጫ በቀረበበት ጊዜም መለያው ያልተሰጠው ከሆነ አመልካቹ በመግለጫው ላይ ይህንኑ መግለጽና መለያው እንደተሰጠ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት ።

፬· አመልካቹ ፓተንት ከመሰጠቱ አስቀድሞ በማንኛውም ጊዜ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) የተገለጸውን መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል ።

፭· በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፪) የተገለጸው የቀዳሚ ማመልከቻ የተረጋገጠ ቅጅ ማቅረቢያ ጊዜ ኮሚሽኑ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ወራት ይሆናል ። ቅጅው ለሌላ ማመልከቻ የተሰጠ ከሆነ አመልካቹ ይህንኑ በማመልከት ምላሽ መስጠት ይችላል ።

፮· ቀዳሚ ማመልከቻው የቀረበው ከእንግሊዝኛ ወይም ከአማርኛ በተለየ ቋንቋ ሲሆን አመልካቹ የቀዳሚ ማመልከቻውን የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ ትርጉም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፭) የተገለፀው ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል ።

፯· ኮሚሽኑ የተለየ ጥያቄ ካላቀረበ በስተቀር የቀዳሚነት ማመልከቻውና ማናቸውም የዚሁ ትርጉም በአንድ ቅጅ ብቻ ይቀርባል ።

፳፩· <u>የውጪ አገር አመልካች</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲ (፪) እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረቡ ሰነዶች የሚያገለግሉት የፓተንት ማመልከቻ የቀረበበትን ፈጠራ አዲስነት እና ፈጠራዊ ብቃት ግምገማ ለማገዝ ብቻ ይሆናል ።

፪· የውጭ አገር አመልካች በዚህ አንቀጽ መሠረት ባቀረባቸው ሰነዶች ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ሊያቀርብ ይችላል ።

፫· በኢትዮጵያ ውስጥ የመኖሪያ ቦታ ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት በሌለው የውጭ ዜጋ ፣ የውጪ ኢንተርፕራይዝ ወይም ሌላ የውጪ ድርጅት ለፓተንት ማመልከቻ ሲቀርብና ኮሚሽኑ ጥርጣሬ ሲያድርበት አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል ፡

ሀ) የአመልካቹን ዜግነት የሚመለከት ሰርተፊኬት ፡

ለ) የውጭ ኢንተርፕራይዙን ወይም ሌላ የውጭ ድርጅቱን ዋና ጽሕፈት ቤት መቀመጫ የሚመለከት ሠርተፊኬት ፡

ሐ) የአንድ የውጭ ዜጋ ፣ የውጭ ኢንተርፕራይዝ ወይም የሌላ የውጭ ሀገር ድርጅት ለዜጎቿ ተፈጻሚ በሚሆንበት መልክ የኢትዮጵያ ዜጎች ወይም ድርጅቶች በሀገሪቱ ፓተንት የማግኘት መብት እንዳላቸው እውቅና የምትሰጥ መሆኑን ማረጋገጫ ።

፳፪· <u>ተዛማጅ የውጪ ማመልከቻ ፣ ፓተንት እና ሌሎች የጥበቃ አይነቶችን አስመልክቶ መረጃ ስለማቅረቢያ ጊዜ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲ መሠረት የተጠየቀ መረጃን የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ወር ማነስ ወይም ከስድስት ወር መብለጥ የለበትም ። ሆኖም በአመልካቹ አሳማኝ ጥያቄ ኮሚሽኑ የጊዜ ገደቡን ሊያሸዝም ይችላል ።

3) Where a symbol of the International Patent Classification has not been allocated to the earlier application, or had not yet been allocated at the time of filing the declaration referred to in sub-Article (1) of this Article, the applicant shall state this fact in the said declaration and shall communicate such symbol as soon as it has been allocated.

4) The applicant may, at any time before the grant of the patent, amend the contents of the declartion referred to in sub-Article (1) of this Article.

5) The period for furnishing the certified copy of the earlier application, referred to in Article 11(2) of the proclamation, shall be three months from the date of the request by the commission; where a copy has already been furnished for another application, the applicant may respond by making a reference to that other application.

6) Where the earlier application is in a language other than English or Amharic, the applicant shall, within six months from the date of the request made under sub-Article 5 of this Article furnish a translation into English or Amharic of the earlier application.

7) Unless the Commission requests otherwise, the earlier application and any translation thereof shall be filed in one copy.

21. *An Applicant From Abroad*

1) Documents furnished pursuant to Article 10(2) of the proclamation and this Article may be used, only for facilitating the evaluation of the novelty and inventive step of the invention for which the patent application is being made.

2) The applicant from abroad may submit comments on any documents furnished by him under this Article.

3) Where an application for a patent is filed by any foreigner, foreign enterprise or other foreign organization having no habitual residence or business office in Ethiopia the commission may, when there is doubt, require the applicant to submit the following documents:

(a) a certificate concerning the nationality of the applicant;

(b) a cerificate concerning the seat of the headquarter of the foreign enterprise or other foreign organzation;

(c) a testimonial showing that the country to which the foreigner, foreign enterprise or other foreign organizatin belongs, recognizes that Ethiopian citizens or entities are, under the same conditions applied to its nationals, entitled to patent rights in that country.

22. *Time for Furnishing Informaion Concerning Corresponding Foreign pplications, Patents and other Titles of Protection*

1) The time limits to be specified for furnishing the information requested under Article 10 of the proclamation shall not be less than two or more than six months from the date such a request is made; upon a reasoned request by the applicant, the Commission may extend such time limit.

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፲ መሠረት የተጠየቁትን ሰነዶች አመልካቹ ሊያገኛቸው እንዳልቻለ መልስ ከሰጠ ኮሚሽኑ የማመልከቻውን ምርመራ ሂደት ሰነዶቹ እስከ ሚቀርቡበት ጊዜ ድረስ ሊያግደው ይችላል ።

፳፫· <u>ማመልከቻን ስለመተው</u>

፩· አንድ ማመልከቻ አመልካቹ በፈረመበትና ለኮሚሽኑ በቀረበ የጽሁፍ መግለጫ ይተዋል ።

፪· ማመልከቻው ቢተውም የማመልከቻ ክፍያው ተመላሽ አይሆንም ።

፳፬· <u>ማመልከቻ ላይ ምልክት ስለማድረግ</u>

፩· ማመልከቻው እንደደረሰ ኮሚሽኑ ማመልከቻው በሚያ ቅፈው እያንዳንዱ ሰነድ ላይ ማመልከቻው የደረሰበትን እርግጠኛ ቀንና ኢት የሚሉ ፊደሎች እዝባር ፣ ፓ የሚል ፊደል እዝባር ፣ የመጀመሪያው ወረቀት የደረሰበት ዓመት የመጨረሻ ሁለት ቁጥሮች እዝባርና ማመልከ ቻዎች ሲደርሱ የሚሰጡ ተከታታይነት ያላቸው ፭ ቁጥሮች የያዘ የማመልከቻ ቁጥር ማስፈር አለበት ። እርማቶቹ ወይም ዘግይተው የገቡ ሰነዶች በሌላ ቀን ሲደርሱ ኮሚሽኑ የደረሱበትን እርግጠኛ ቀን አግባብ ባለው ቦታ የፓተንት ጥያቄ በቀረበበት ሰነድ (ቅጽ ቁጥር ዜሮ ፩) ላይ ያሰፍራል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለማመልከቻ የተሰጠ ቁጥር ማመልከቻውን አስመልክቶ በሚደረግ የደብዳቤ ልውውጥ ላይ መጠቀስ አለበት ።

፳፭· <u>የምዝገባ ቀን መስጠት እና ማሳወቅ</u>

፩· ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ለመስጠት ማመልከቻው የአዋጁን አንቀጽ ፲፪(፩) መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን ይመረምራል ።

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፪) መሠረት የሚቀርብ ማናቸውም ማሻሻያ የማቅረብ ጥሪ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ተፈላጊውን ማሻሻያ መግለጽና ማሻሻያው ጥሪው ከተደ ረገበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከተመደበው ክፍያ ጋር እንዲቀርብ መጠየቅ አለበት ።

፫· ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ከሰጠ በኋላ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል ። ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፪) መሠረት ማመልከቻው እንዳልቀረበ የተቆጠረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ለአመልካቹ ምክንያቶችን በመዘርዘር በጽሁፍ ያሳውቃል ።

<u>ክፍል ፪</u>
<u>ስለማመልከቻ ምርመራ</u>

፳፮· <u>መርማሪ ከመሆን ስለመገለል</u>

አንድ መርማሪ በራሱ ፍላጎት ፣ ወይም በአመልካቹ ወይም በሌላ ማናቸውም ጉዳዩ በሚመለከተው ወገን በሚቀርብ ጥያቄ ከምርመራ ሥራው የሚገለለው ፣

፩· ከአመልካቹ ወይም ከፓተንት ወኪሉ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለው ሆኖ ሲገኝ ፣

፪· በፓተንት ማመልከቻው ላይ ጥቅም ያለው ሲሆን ፣

፫· ከአመልካቹ ወይም ከፓተንት ወኪሉ ጋር ያለው ማንኛውም ሌላ አይነት ግንኙነት አድሎአዊ ያልሆነ የማመልከቻ ምርመራ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል ሆኖ ሲገኝ ይሆናል ።

፳፯· <u>የፎርማሊቲ ምርመራ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፱(፫) ና (፬) (ሀ) እና ይህንኑ በተመለከተ በደንቡ ከተገለጹት መሟላት ከሚገባቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የአዋጁ አንቀጽ ፭፡፯፡፱(፯) እና (፰) እንዲሁም ፲ ለአዋጁ ዓላማ ፎርማሊቲን አስመልክቶ መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ተደርገው ይወሰዳሉ ።

2) If the applicant replies that the documents requested under Article 10 of the proclamation are not yet available, the Commission may suspend the procedure for the exmination of application until such time as the documents are furnished.

23. *Withdrawal of Application*

1) An application shall be withdrawn by written declaration submitted to the Commission and signed by the applicant.

2) The application fee shall not be refunded if the application is withdrawn.

24. *Marking Application*

1) Upon receipt, the Commission shall mark, on each document making up the application, the actual date of receipt and the application number consisting of the letters ET, slant, the letter P, slant, the last two numbers of the year in which the initial papers were received, slant, and a five digit number allotted in the sequential order in which applications are received; where any corrections or other later filed documents are received on different dates, the Commission shall also mark their actual date of receipt in the appropriate place of the request for grant of the patent (Form No 1).

2) The application number allotted under sub-Article (1) of this Article shall be quoted in all subsequent communications concerning the application.

25. *According and Notifying Filing Date*

1) The Commission shall examine, in order to accord a filing date, whether the application fulfills the requirements of Article 12 (1) of the proclamation.

2) The invitation to file any correction, under Article 12 (2) of the proclamation, shall be in writing, it shall specify the correction or corrections required and request that these be filed within two months from the date of the invitation, together with the payment of the prescribed fee.

3) Once the Commission accords a filing date, it shall notify the applicant in writing; if the application is treated as if it had not been filed, under Article 12 (2) of the proclamation, the Commission shall notify the applicant in writing specifying the reasons.

SECTION TWO
Examination Of Application

26. *Exclusion From Being Examiner*

An examiner shall, on his own initiative or upon the request of the applicant or any other interested party, be excluded from exercising his function where, he

1) is a close relative of the applicant or the patent agent,

2) has an interest in the application for patent, or

3) has such other kinds of relations with the applicant or the patent agent that might influence the impartial examination of the application.

27. *Examination as to Form*

1) In addition to the requirements of Article 9 (3) and (4) (a) of the proclamation and the Regulations pertaining thereto, the requirements of Articles 5,8,9(7) and (8) and 10 of the proclamation shall be considered formal requirements for the purpose of the proclamation.

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ (፪) እና በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ኮሚሽኑ አመልካቹን በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ማሻሻያ ከተመደበው ክፍያ ጋር እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይጠራዋል ።

፫· አመልካቹ የተጓደለውን ለማሟላት በተደረገው ጥሪ መሰረት ምላሽ ያላቀረበ ሲሆን ወይም አመልካቹ ማሻሻያ ያቀረበ ቢሆንም በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ(፩) የተገለጹት ሁኔታዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ሲያምን ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ለአመልካቹ ምክንያቱን ገልጾ በጽሁፍ ያሳውቃል ።

፬· የማመልከቻው ውድቅ መሆን የምዝገባውን ቀን ተቀባ ይነት አያሳጣውም ።

፳፰· <u>የሥረ-ነገር ምርመራ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲፫(፫) መሠረት ኮሚሽኑ በሚሰይ ማቸው ልምድ ባላቸው የቴክኒክና የህግ ኤክስፐርቶች አማካኝነት የሥረ-ነገር ምርመራ ይከናወናል ።

፪· የፍለጋና የምርመራ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ኮሚሽኑ ማመልከቻውን አግባብ ካላቸው ሰነዶች ጋር በማያያዝ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫(፫) መሠረት የሚከናወነውን የምርመራ ተግባር በተመለከተ ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት ላደረገ የምርመራ ባለሥልጣን መላክና የፍለጋና የምርመራ ዘገባ እንዲላክለት መጠየቅ ይችላል።

፫· አንድ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፫ ፣ ፬ ፣ ፯ ፣ ፱(፪) (፬) (ለ) (ሐ) እና (፭) እና አግባብነት ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑን ይመረመራል።

፬· ኮሚሽኑ የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ውጤትን ግምት ውስጥ በማስገባት በአዋጁ እና በዚህ ደንብ የተገለፀት መመዘኛዎች ያልተሟሉ መሆናቸውን ሲያምን አመል ካቹን በመጥራት (አስፈላጊ ከሆነ ጥሪው ተደጋጋሚ ሊሆን ይችላል) ማመልከቻውን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አሻሽሎ ወይም ከፋፍሎ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይጠይቀዋል ። የጊዜ ገደቡ ለአመልካቹ ጥሪ ከሚደረ ግበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ወር ያላነሰ ወይም ከስድስት ወር ያልበለጠ ይሆናል ። ጥሪውም የሚከናወነው በቅጽ ፪ መሠረት ነው ።

፭· በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ (፬) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ መሠረት የሚደረግ ማናቸውም ማሻሻያ ከተወሰነለት ክፍያ ጋር መከናወን አለበት ።

፮· አመልካቹ በጥሪው መሠረት ተገቢውን ሳያደርግ ሲቀር ወይም አመልካቹ ያቀረበው ማንኛውም አስተያየት ፡ ማሻሻያ ወይም ክፍፍል የምርመራና ፍለጋ ሪፖርቱን ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲታይ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተዘረዘሩ ሁኔታዎችን የማያሟላ መሆኑ ሲታመን ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል ። ይህንኑም ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል ።

<u>ክፍል ፫</u>
<u>ፓተንት ስለመስጠትና ስለፓተንት ይዘት</u>

፳፱· <u>ፓተንት የመሰጠት ወይም የመከልከል ውሳኔ</u>

፩· ተመሳሳይ የምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ተመሳሳይ የቀዳሚነት ቀን ያላቸው አንድን ፈጠራ የሚመለከቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማመልከቻዎች በአንድ አመልካች ሲቀርቡ ኮሚሽኑ በዚሁ ምክንያት ከአንድ በላይ ለሆኑ ማመልከቻዎች ፓተንት አልሰጥም ብሎ መከልከል ይችላል ።

2) Where the commission finds that the conditions referred to in Article 13 (1) of the proclamation and sub-Article (1) of this Article are not fulfilled it shall invite the applicant, in writing, to file the required correction within two months from the date of the invitation, together with the payment of the prescribed fee.

3) Where the applicant does not comply with the invitation to correct a deficiency, or where despite the corrections submitted by the applicant, the Commission is of the opinion that the conditions referred to in sub-Article (1) of this Article are not fulfilled, it shall reject the application and notify the applicant, in writing, stating the reasons.

4) Refusal of the application shall not affect its filing date which shall remain valid.

28. *Examination as to Substance*

1) Subject to Article 13 (3) of the proclamation, substantive examination shall be undertaken by experienced technical and legal experts designated by the Commission.

2) Subject to the payment of the prescribed search and examination fee, the Commission may, for the purpose of the examination under Article 13 (3), transmit the application, together with all relevant documents, to an examining authority which has concluded an arrangement to this effect with the Commission, requesting a search and examination report.

3) An application shall be examined as to whether the requirements of Articles 3,4,7,9(2),(4)(b) and (c) and (5) of the proclamation and the Regulations pertaining thereto are fulfilled.

4) Where, taking due account of the conclusions of the search and examination report, the Commission is of the opinion that the conditions referred to in the proclamation are not fulfilled, it shall notify the applicant in writing, inviting him, several times if necessary, to amend or divide his application within a specified period; such specified period shall not be less than two or more than six months from the date of the invitation. The invitation shall be made on Form No. 2.

5) Any amendment under sub-Article (4) of this Article and under Article 18 of these regulations shall be made together with the prescribed fee.

6) Where the applicant does not comply with the said invitation or where, despite any observation, amendment or division submitted by the applicant, the Commission, taking due account of the conclusions of the search and examination report, is of the opinion that the conditions referred to in the proclamation and these Regulations are not fulfilled, it shall reject the application and notify the applicant of the same in writting.

SECTION THREE
Issuance and Contents of Patents

29. *Decision to Grant or Refuse to Grant Patent*

1) Where two or more applications for grant of a patent for the same invention, having the same filing or, where applicable, the same priority date, are filed by the same applicant, the Commission may, on that ground, refuse to grant a patent in pursuance of more than one of the applications.

ፎ. ኮሚሽኑ የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ውጤትን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ የተጠቀሰውን መሠረት በማድረግ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ (፫) ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያምን ፓተንት ይሰጣል ።

ፐ. ኮሚሽኑ ፓተንት ለመስጠት ወይም ለመከልከል የሰጠውን ውሳኔ ለውሳኔው መሠረት ከሆነው የፍለጋና ምርመራ ሪፖርት ቅጅ ጋር በማያያዝ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል ። በተጨማሪም ውሳኔው የፓተንት መሰጠትን የሚከለክል ሲሆን ዝርዝር ምክንያቶቹ መገለጽ አለባቸው ። ውሳኔው ፓተንት ለመስጠት ሲሆን አመልካቹ ውሳኔውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ የፓተንትና የህትመት ክፍያ እንዲፈጽም ይጠይቃል ።

፴. <u>ፓተንት ስለመስጠት</u>

፩. የፓተንትና የህትመት ክፍያ ፓተንት ለመስጠት መወሰኑ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ የተከፈለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፩) እና በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት ኮሚሽኑ ፓተንት ይሰጣል።

፪. ኮሚሽኑ ለእያንዳንዱ ለሚሰጠው ፓተንት እንደ አሰጣጡ ቅደም ተከተል የፓተንት የህትመት ቁጥር ይሰጣል ።

፫. ፓተንቱ ፡

ሀ) በቅጽ ቁጥር ፫ መሠረት የሚሰጥና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) ከተገለጸው መረጃ በተጨማሪ የፓተንቱን ህትመት ቀን ፡ በቀደምት ጥበብ የተመለከቱ ሰነዶች ዋቢዎች ፡ የፈጠራው መግለጫ ፡ የመብት ወሰንና ካለም ስዕሎችን ያካትታል ፤

ለ) እንደተሰጠ የሚገመተው ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፪)(ሀ) ስለፓተንቱ መሰጠት ጠቅሶ በህትመት ባወጣበት ቀን ነው ።

፴፩. <u>ፓተንት ስለመሰጠቱ ጠቅሶ ስለማተም</u>

ፓተንት ስለመሰጠቱ ተጠቅሶ የሚወጣ ህትመት ፡

፩. የፓተንቱን ቁጥር ፡

፪. የፓተንት ባለቤቱን ስምና አድራሻ ፡

፫. በፓተንቱ ውስጥ ስሙ እንዳይጠቀስ ካልጠየቀ በስተቀር የፈጠራ ሰራተኛውን ስምና አድራሻ ፡

፬. በኖረ ጊዜ የወኪሉን ስምና አድራሻ ፡

፭. የማመልከቻውን የምዝገባ ቀንና ቁጥር ፡

፮. ቀዳሚነት ከተጠየቀና ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ቀዳሚነቱን የሚመለከት መግለጫ ፡ የቀዳሚነት ቀንና ቀዳሚው ማመልከቻ የገባበትን ሀገር ወይም ሀገሮች ስም ፡

፯. ፓተንት የተሰጠበትን ትክክለኛ ቀን ፡

፰. የፈጠራውን ርዕስ ፡

፱. የፈጠራውን አጭር ይዘት ፡

፲. በኖረ ጊዜ ከስዕሎቹ መካከል በይበልጥ ገላጭ የሆነውን እንዲሁም ፡

፲፩. የዓለም አቀፍ ፓተንት ምደባ ምልክትን ማካተት አለበት ።

፴፪. <u>የፓተንት ሰርተፊኬት ስለመስጠት</u>

የፓተንት መሰጠት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በቅጽ ቁጥር ፬ ላይ መዘጋጀት ፡ በኮሚሽኑ መፈረምና፡

፩. የፓተንቱን ቁጥር፡

2) Where the Commission, taking due account of the conclusions of the search and examination report, is of the opinion, subject to Article 28 of these Regulations, that the conditions referred to in Article 13(3) of the proclamation are fulfilled, it shall grant a patent.

3) The Commission shall notify the applicant, in writing, of its decision to grant or to refuse to grant a patent, attaching a copy of the search and examination report upon which the decision is based and, in the case of a refusal, stating the reasons therefor, and in the case of a decision to grant a patent, requesting the applicant to pay the grant and publication fee within three months from the date of the notification.

30. *Grant of Patent*

1) When the payment of the grant and publication fee is made within three months from the date of the notification of the decision to grant the patent, the Commission shall grant the patent in accordance with Article 14 (1) of the proclamation and the provisions of this Article.

2) The Commission shall allot to each patent it grants a Patent publication number in the sequential order of the grant.

3) The patent shall be:

(a) granted on Form No 3 and shall contain in addition to the information indicated under sub-Article (2) of this Article the date of publication of the patent, the documents or references cited of the prior art, the description, the claims and the drawings, if any,

(b) deemed to be granted on the date the Commission publishes and reference to the grant in accordance with Article 14 (2) (a) of the proclamation.

31. *Publication of Reference to the Grant of Patent*

The publication of the reference to the grant of the patent shall include:

1) the number of the patent,
2) the name and address of the owner of the patent,
3) the name and address of the inventor, except where he has asked not to be named in the patent,
4) the name and address of the agent, if any,
5) the filing date and number of the application,
6) if priority has been claimed and the claim has been accepted, a statement of the priority, the priority date and the name of the country or countries in which or for which the earlier application was filed,
7) the effective date of grant of the patent,
8) the title of the invention,
9) the abstract,
10) the most illustrative of the drawings, if any, and
11) the symbol of the International Patent Classification.

32. *Issuance of Certificate of Grant of Patent*

The certificate of grant of a patent shall be issued on Form No 4, shall be signed by the commissioner and shall contain:

1) the number of the patent,

፪. የፓተንት ባለቤቱን ስምና አድራሻ፣
፫. የምዝገባውን ቀንና እንደአግባቡ የማመልከቻውን የቀዳሚነት ቀን፣
፬. ፓተንት የተሰጠበትን ትክክለኛ ቀንእና፣
፭. የፈጠራውን ርዕስ ማካተት አለበት ።

፴፫. ስለፓተንት መብት መራዘም

በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የፓተንት መብት ጥበቃ ዘመን የማራዘም ጥያቄ በጽሁፍ ለኮሚሽኑ መቅረብና ፈጠራው በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ የዋለበትን ዝርዝር ሁኔታ ከሚገልጽ በፓተንት ባለቤቱ የተፈረመበት መግለጫ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል ።

ክፍል ፬
ፈቃድ በተሰጠው ሰው በፓተንት የሚጠበቅን ፈጠራ ጥቅም ላይ ስለማዋል

፴፬. በፓተንት የሚጠበቅን ፈጠራ በመንግሥት ወይም በመንግሥት ሥልጣን በተሰጣቸው ሦስተኛ ወገኖች ጥቅም ላይ ስለማዋል

፩. ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፪) መሠረት ውሳኔ ከመስጠቱ አስቀድሞ ለባለፓተንቱ ፣ ለግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች እና ለማንኛውም ተሳትፎው ጠቃሚ ይሆናል ብሎ ለሚገምተው ወገን ጉዳያቸው ከሚሰማበት ቀን በፊት ቢያንስ ሀያ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት ። ባለፓተንቱ ፓተንቱን በፈቃድ ለወሰዱ ወገኖች በሙሉ የጉዳዩን መሰማት አስመልክቶ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት ያለበት ሲሆን እነሱም በጉዳዩ የመሳተፍ መብት አላቸው ።
፪. ኮሚሽኑ ጉዳዩን ካየ በኋላ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸውን ነጥቦች እና ፈጠራው በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፪) መሠረት አገልግሎት ላይ እንዲውል ከወሰነ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ በጽሑፍ መግለጽ አለበት ።
፫. ኮሚሽኑ ውሳኔውን መመዝገብ ፣ ማሳተም እንዲሁም ባለፓተንቱ እና ሌሎች በጉዳዩ የገቡ ወገኖች በጽሑፍ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት ።
፬. ኮሚሽኑ የመጠቀሚያ ክፍያን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ከተጠየቀበት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የፍርድ ቤቱን የመጨረሻውን የይግባኝ ውሳኔ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት ። ኮሚሽኑም ውሳኔውን ይመዘግባል ፣ በሕትመት ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል ።

፴፭. የግዴታ ፈቃድ ጥያቄ

በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ የግዴታ ፈቃድ ጥያቄ በቅፅ ቁጥር ፮ ተሞልቶ ከተመደበው ክፍያ ጋር እና ፣

፩. ፈጠራው በሌላ ፓተንት በተሰጠው ፈጠራ ላይ ጥገኛ መሆኑንና ይህንኑ ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ካልተጠቀመ ፈጠራውን ለመጠቀም እንደሚያስቸግር ከሚገልጽ ማስረጃ ፣
፪. ባለፓተንቱ ከግዴታ ፈቃድ ጠያቂው የፈቃድ ውል ጥያቄ የደረሰው መሆኑንና የግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ፈቃዱን በተገቢው ሁኔታና ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ያልቻለ መሆኑን ከሚገልጽ ማስረጃ ፣

2) the name and address of the owner of the patent,
3) the filing date and, where applicable, priority date of the application,
4) the effective date of grant of the patent, and
5) the title of the invention.

33. *Extension of Duration of a Patent*

The request to extend the duration of a patent, under Article 16 of the proclamation, shall be made in writing to the Commission, and shall be accompanied by a statement signed by the owner of the patent setting out particulars of the working of the invention in Ethiopia.

SECTION FOUR
Exploitation of Patented Invention by Authorized Persons

34. *Exploitation of Patented Invention by Government or by Third Persons Authorized by Government*

1) The Commission shall, before making a decision under Article 25 (2) of the proclamation, give the patentee, beneficiaries of compulsory licenses, and any other persons whose participation it considers useful, at least 21 days written notice of the date on which they may be heard; the patentee shall give all licensees written notice of the hearing and they shall have the right to participate therein.
2) The Commission shall make its decision, after the hearing in writing, stating the grounds upon which it is based, and, if it has decided that the invention shall be exploited under Article 25 (2) of the proclamation, stating the terms of the exploitation.
3) The Commission shall record and publish the decision and notify, in writing, the patentee and other participants in the hearing.
4) If the decision of the Commission with regard to remuneration is the subject of an appeal, the registrar of the court shall notify the commission of the court's decision once it becomes final and the commission shall record the decision and publish it.

35. *Request for Compulsory Licenses*

The request for grant of a compulsory licence, under Article 29 of the proclamation, shall be made to the Commission on Form No. 6, together with the payment of the prescribed fee; it shall be accompanied by:

1) evidence that his invention is dependent on a patented invention and that it is difficult to make use of it without the use of the latter,
2) evidence that the patentee has received a request, from the person requesting the compulsory licence, for a licence contract but that the latter has been unable to obtain such a licence on reasonable terms and within a reasonable time, and

፫. የግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ በስራ ላይ ለማዋል የተለመውን የስራ እቅድ ፈጠራውን በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ለማዋል ብቃት እንዳለው ከሚገልጽ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል ።

፴፮. የግዴታ ፈቃድ ጥያቄን ስለመቀበል ወይም አለመቀበል

፩. ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉ ሦስት ወራት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፭ የተገለጹት ሁኔታዎች ጠቅለል• ባለ አኳኋን መሟላታቸውና አለመሟላታቸውን ይመረምራል ።

፪. ኮሚሽኑ በምርመራው ወቅት ፣

ሀ) መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ያልተሟሉ ሆኖ ሲያገኝ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበው ግለሰብ ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል ፣

ለ) መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ተሟልተው ሲያገኝ ወዲያውኑ ለባለፓተንቱ ፣ ለግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች እና በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፪) መሠረት ፓተንት የተሰጠበትን ፈጠራ ጥቅም ላይ ላዋሉ ሰዎች የጥያቄውን ቅጅ መላክና ጥሪው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ያላቸውን አስተያየት ለኮሚሽኑ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ መጋበዝ አለበት ።

፫. ባለፓተንቱ ወዲያውኑ ለሁሉም ፈቃድ ተቀባዮች ስለጥያቄው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት ። ፈቃድ ተቀባዮቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ጥሪ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ ያላቸውን አስተያየት በጽሑፍ የማቅረብ መብት አላቸው ።

፬. ኮሚሽኑ ለግዴታ ፈቃድ ጠያቂው ወዲያውኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የቀረቡትን አስተያየቶች ያሳውቃል ።

፭. ኮሚሽኑ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን የግዴታ ፈቃድ የጠየቀውን ግለሰብ ፣ ባለፓተንቱን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት አስተያየታቸውን ያቀረቡ ግለሰቦች ይጠራል ይህንኑም ጉዳዩ የሚሰማበት ቀን ከመድረሱ ከአንድ ወር በፊት በጽሑፍ ያሳውቃል ።

፴፯. የግዴታ ፈቃድ የመስጠት ወይም የመከልከል ውሣኔ

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፮(፭) መሠረት ጉዳዩ ከተሰማ በኋላ ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት የሚያበቁት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ይሰጣል ፣ ካልሆነ ግን ይከለክላል ።

፪. የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል የተሰጠው ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ለውሳኔው መሰረት የሆኑትን ምክንያቶች መያዝ ይኖርበታል ውሳኔው የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ሲሆን ፣

ሀ) ፈቃድ የተሰጠበትን ጊዜ ገደብ፣

ለ) ፈቃዱ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪(፩) ከተገለጹት ተግባራት የትኞቹን እንደሚሸፍን ፣

ሐ) የግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚው ፓተንት የተሰጠውን ፈጠራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጀመር በትን የጊዜ ገደብ ፣ እንዲሁም

መ) የመጠቀሚያ ክፍያ አፈፃፀም ሁኔታዎችን መዘርዘር አለበት ።

3) an indication of the plan according to which the person requesting the compulsory licence intends to work the patented invention, including evidence that he has the ability to do so in Ethiopia.

36. *Acceptance or Refusal of Request for Comulsory Licence*

1) The Commission shall, within three months from the date of the request of grant of a compulsory licence, examine whether the requirements of Article 29 of the proclamation and Article 35 of these Regulations are Primafacie satisfied.

2) Where the Commission, upon examination,
   (a) finds that the requirements are not satisfied, it shall reject the request and, in writing, notify the person requesting the compulsory licence,
   (b) finds that the requirements are satisfied, it shall forth with send a copy of the request to the patentee, the beneficiaries of compulsory licence and to persons exploiting the patented invention under Article 25 (2) of the proclamation, and invite them to submit observation thereon, in writing, to the Commission within three months from the date of the invitation.

3) The patentee shall forthwith, in writing, notify all licensees of the request, and the licensees shall have the right to submit observations theron, in writing, to the Commission within three months of the date of the invitation issued under sub-Article (2) of this Article.

4) The Commission shall forthwith notify the person requesting the compulsory licence of any observations submitted under sub-Article (2) and (3) of this Article.

5) The Commission shall then convene a hearing to which it shall invite the person requesting the compulsory licence, the patentee and the persons who submitted observations under sub-Article (2) and (3) of this Article giving them at least one month's written notice of the date set for the hearing.

37. *Decision to Grant or Refuse Compulsory Licence*

1) After the hearing, under Article 36(5) of these Regulations,if the Commission finds that the conditions for the grant of a compulsory licence are fulfilled, it shall grant the licence, other wise, it shall refuse it.

2) The decision to grant or to refuse a compulsory licence shall be in writing shall state the grounds upon which it is based and, in the case of a decision to grant the compulsory licence, shall specify, in particular,
   (a) the period for which the licence is granted,
   (b) to which of the acts referred to in Article 22 (1) of the proclamation the licence extends.
   (c) the time limit within which the beneficiary of the compulsory licence must commence working the patented invention, and
   (d) the terms regarding payment of remuneration.

፫. ኮሚሽኑ የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል የደረሰበትን ውሳኔ በመመዝገብ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል ። የውሳኔውን ቅጅ የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጠው ለጠየቀው ሰው ፣ ለባለፓተንቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፯(፪) እና (፫) መሠረት አስተያየታቸውን ላቀረቡ ሰዎች ይልካል ።

፴፰. ስለፓተንት መሰረዝ

፩. የአዋጁ አንቀጽ ፴፮(፩) ድንጋጌ ተፈፃሚነት በተወሰኑ የጥበቃ ወሰን ጥያቄዎች ላይ ብቻ ወይም በተወሰኑ የጥበቃ ወሰን ጥያቄ አካሎች ላይ ሲሆን እነኝህ የጥበቃ ወሰን ጥያቄዎች ወይም የጥበቃ ወሰን አካሎች ይሰረዛሉ ።

፪. ባለፓተንቱ የፓተንት መሰረዝን አስመልክቶ በፍርድ ቤት ስለተጀመረ ጉዳይ ለማንኛውም ፈቃድ ተቀባይ በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት ። የፓተንት ስረዛን ጥያቄ ያቀረበው ወገን በአዋጁ አንቀጽ ፴ መሠረት ለተሰጠ የግዴታ ፈቃድ ተጠቃሚዎች በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን ለፓተንቱ መሰረዝ የቀረበው ምክንያት ባለፓተንቱ ወይም የእርሱ ወራሽ የፈጠራው ሠራተኛ ወይም የሱ ሕጋዊ ወራሽ አይደለም በሚል ከሆነ በፓተንቱ ላይ መብት አለው ለሚባል ወገን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት ።

ምዕራፍ ፫
ስለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት

፴፱. ከፓተንት ጋር ስለተዛመዱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት

፩. የአዋጁ አንቀፅ ፫(፩) ፣ (፫) እና (፬) በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ።

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ።

፫. አንድ ጉዳይ የአዋጁን አንቀፅ ፵፭ ከአንቀፅ ፴፮ ጋር በማጣመር በሚታይበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትን ይሰርዛል ፤

ሀ) የአዋጁ አንቀፅ ፴፱ እና ፵፭ ድንጋጌዎች ከአንቀፅ ፫(፭) ጋር በመጣመር ሲታዩ ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ፈጠራ ለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ብቁ ሳይሆን ፤

ለ) የፈጠራው መግለጫና የመብት ወሰን ጥያቄዎች አንቀፅ ፵፭ ፣ አንቀጽ ፱(፬) (ለ) እና (ሐ) እና ከዚሁ ጋር በሚዛመዱ ደንቦች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የማያሟሉ ሲሆን ፤

ሐ) ፈጠራውን ለመረዳት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም ሥዕል ሳይቀርብ ሲቀር ፤

መ) የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀቱ ባለቤት የፈጠራ ሠራተኛው ወይም የሱ ሕጋዊ ወራሽ ሳይሆን ፤

ሠ) በአዋጁ አንቀፅ ፴ መሠረት ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ፈጠራ ለጥበቃ ብቁ ያልነበረ ሲሆን ።

፬. ከዚህ በታች የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ ምዕራፍ ሁለት በተዘረዘሩት አንቀጾች የተገለፁት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ፤

ሀ) በደንቡ አንቀፅ ፷፬ ላይ የተገለጸው ፊደል "ፓ" "ግልሞ" ሆኖ እንዲነበብ፤

3) The Commission record and publish the decision to grant or to refuse the compulsory licence and transmit a copy thereof to the person requesting the compulsory licence, the patentee and the persons who submitted observations under Article 36 (2) and (3) of the Regulations.

38. *Invalidation*

1) Where the provisions of Article 36 (1) of the proclamation apply only to some of the claims or some parts of a claim, such claims or parts of a claim shall be invalidated.

2) The patentee shall, in writing, notify any licensee of any court proceeding instituted for the invalidation of the patent; the person requesting invalidation shall so notify beneficiaries of compulsory licenses granted under Article 30 of the proclamation and, where the ground of invalidity invoked is that the patentee is not the inventor or his successor in title, also the person alleged to have the right to the patent.

CHAPTER THREE
Utility Model Certificates

39. *Application of Provisions Relating to Patents*

1) Articles 3(1), (3) and (4) of the proclamation shall not apply in the case of applications for utility model certificates.

2) Article 16 of the proclamation shall not apply in the case of utility model certificates.

3) In proceedings under Article 45 in conjunction with Article 36 of the proclamation, the court shall invalidate the utility model certificate on the grounds that:

(a) the claimed invention did not qualify for a utility model certificate having regard to the provisions of Articles 39 and 45 in conjunction with Article 3(5) of the proclamation,

(b) the description and the claims do not comply with the requirements prescribed by Article 45 in conjunction with Article 9(4) (b) and (c) of the proclamation and the regulations pertaining thereto,

(c) any drawing which is necessary for the understanding of the invention has not been furnished,

(d) the owner of the utility model certificate is not the inventor or his successor in title, or

(e) the claimed invention did not qualify for protection under Article 40 of the proclamation.

4) The provisions of the Articles set out in chapter II of these Regulations shall apply, mutatis mutandis to utility model certificates, subject to the following exceptions:

(a) the letter P, in Article 24 of the Regulations shall be read as the letters UM,

ለ) የዚህ ደንብ አንቀፅ ፳፰ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣ እንዲሁም

ሐ) በደንቡ አንቀጽ ፴፰ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ ፴፮(፩) ፣ የአዋጁን አንቀጽ ፵፫ እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)ን የሚጠቅስ ሆኖ ይነበባል ።

፭· በአዋጁ አንቀጽ ፵፫ መሠረት የሚቀርብ የፓተንትና የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን የማለዋወጥ ጥያቄ በአመልካቹ ተፈርሞ ከተመደበው ክፍያ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት ። ጥያቄው በቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ኮሚሽኑ ውሳኔውን በጽሑፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ እና ጥያቄውን ካልተቀበለ ምክን ያቱን መግለጽ አለበት ።

ምዕራፍ ፬
ስለኢንዱስትሪያዊ ንድፎች

፵· ከፓተንት ጋር ስለተዛመዱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት

የዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ፣ ፭፫ እና ፭፬ እንደአግባብነቱ በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ፣ ለዚሁ ሲባል በዚሁ ደንብ አንቀጽ ፭፬(፩) የተገለጸው ፊደል "ፓ" "ኢን" ተብሎ ይነበባል ።

፵፩· ኢንዱስትሪያዊ ንድፍን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ

፩· ኢንዱስትሪያዊ ንድፍን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በቅጽ ቁጥር ፯ ተሞልቶ በእያንዳንዱ አመልካች መፈረም አለበት ።

፪· ማመልከቻው የእያንዳንዱን አመልካች ስም ፣ አድራሻ፣ ዜግነትና መኖሪያ መያዝ ይኖርበታል ።

፫· አመልካቹ ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ያመነጨው ሰው ከሆነ ጥያቄው ይህንኑ የሚያመለክት መግለጫ መያዝ አለበት ። አመልካቹ ሌላ ሰው ከሆነ ጥያቄው የእያንዳንዱን የፈጠራ ሠራተኛ ስምና አድራሻ ማመልከትና አመልካቹ ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን በስሙ ለማስመዝገብ ባለመብት መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ መያዝ ይኖርበታል ።

፬· አመልካቹ በወኪል የተወከለ ከሆነ ጥያቄው ይህንኑ ማመልከትና የወኪሉን ስምና አድራሻ መያዝ ይኖርበታል ።

፵፪· ስለመግለጫዎችና ስለናሙናዎች ብዛትና መጠን

፩· የሚከተሉት ከማመልከቻው ጋር መያያዝ አለባቸው ፤

ሀ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ባለ ሁለት ገጽታ ከሆነ አራት ግራፊክ መግለጫዎች ወይም አራት ሥዕሎች ፣ ወይም ንድፎች ፣ ወይም

ለ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ባለሦስት ገጽታ ከሆነ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ እያንዳንዱ የተለያዩ ጎኖች አራት ግራፊክ መግለጫዎች ወይም አራት ሥእሎች ወይም ንድፎች ፣ እና

ሐ) የሕትመት መጠኑ በኮሚሽኑ ተገቢ ነው ተብሎ የሚወሰን የማተሚያ ቅርጽ ወይም የማተሚያ ቅርጾች ።

፪· የናሙና መጠን ከ፳ ሴ·ሜ × ፳ ሴ·ሜ × ፳ ሴ·ሜ መብለጥ የለበትም ። ማንኛውም የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የግራፊክ መግለጫ ፣ ሥዕል ወይም ንድፍ ከ፲ ሴ·ሜ × ፳ ሴ·ሜ መብለጥ የለበትም ። መግለጫዎቹ ፣ ሥእሎቹ ወይም ንድፎቹ የኤ፬ መጠን ባላቸው ጠንካራና ረጅም እድሜ በሚቆዩ አራት ወረቀቶች ላይ መለጠፍ ይኖርባቸዋል ። ሥዕሎችና ንድፎች በጥቁር ቀለም መሠራት አለባቸው ።

(b) Article 28 of these regulations shall not apply, and

(c) the reference in Article 38 of these Regulations to Article 36(1) of the proclamation shall be read as a reference to Article 45 of the proclamation and sub-Article (3) of this Article.

5) A request, under Article 43 of the proclamaion, for the conversion of an application for a patent into an application for a utility model certificate, or vice versa, shall be signed by the applicant and shall be accompanied by the prescribed fee. The Commission shall within two months of the receipt of the request notify the applicant of its decision thereon, in writing, and where it refuses the request, it shall state the reasons.

CHAPTER FOUR

Industrial Designs

40. *Application of Provisions Relating to Patents*

Articles 20, 23 and 24 of these Regulations shall apply mutatis mutandis to industrial designs and for this purpose the letter P, in Article 24(1) of these Regulations, shall be read as the letters ID.

41. *Application for Registration of an Industrial Design*

1) The application for registration of an industrial design shall be made on Form No.7 and shall be signed by each applicant.

2) The application shall indicate each applicant's name, address, nationality, and residence.

3) Where the applicant is the creator, the request shall contain a statement to that effect, and where he is not, it shall indicate each creator's name and address and be accompanied by the statement justifying the applicant's right to the registration of the industrial design.

4) If the applicant is represented by an agent, the request shall so indicate and state the agent's name and address.

42. *Number and Size of Representations and specimen*

1) The application shall be accompanied by the following:

(a) if the industrial design is two-dimensional, by four graphic representations or four drawings or tracings; or

(b) if the industrial design is three-dimensional, by four graphic representations or four drawings or tracings of each of the different sides of the industrial design; and

(c) a printing block or printing blocks of such dimensions as the Commission may consider appropriate.

2) A specimen shall be of a size not exceeding 20 centimetres x 20 centimetres x 20 centimetres. No graphic representation, drawing or tracing of the industrial design shall exceed 10 centimetres x 20 centimetres. Such representations, drawings or tracings, shall be affixed on four sheets of hard and durable paper of A4 size. drawings and tracings shall be made in black ink.

፵፫· የምዝገባ ቀን ስለመስጠት ፣ ስለማሳወቅ እና ምርመራ

፩· ኮሚሽኑ ማመልከቻውን በተቀበለበት ጊዜ ማመልከቻው ያመልካቹን ማንነት ለማረጋገጥ የሚረዳ ጥቆማ እና ተፈላጊውን ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ያካተተውን እቃ ግራፊክ መግለጫ የያዘ ሲሆን ማመልከቻውን የተቀበለበትን ቀን የምዝገባ ቀን አድርጎ ይወስደዋል ። የአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፪) እንደአግባቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፪) እና ፶፩ እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማናቸውም የማሻሻያ ጥሪ በጽሑፍ ሆኖ ጥያቄው የሚፈለገውን ማሻሻያ ወይም ማሻሻያዎች ምንነት ይዘ ከተመደበው ክፍያ ጋር በሁለት ወር ውስጥ እንዲቀርብ የሚጠይቅ መሆን አለበት ።

፫· ኮሚሽኑ የምዝገባ ቀን ከሰጠ በኋላ ይህንኑ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት ። ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፪) እና አንቀጽ ፶፩ እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከመጀመሪያ እንዳልቀረበ ከተቆጠረ ኮሚሽኑ ምክንያቶቹን በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት ።

፬· ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ ፵፰(፩) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፩ እና ፵፪ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አለመሟላታቸውን ሲያረጋግጥ አመልካቹ ተፈላጊውን ማሻሻያ ከተመደበው ክፍያ ጋር ከጥሪው ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ እንዲያቀርብ በጽሑፍ ይጠራዋል። አመልካቹ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጉድለቱን ሳያርም ሲቀር ወይም እርማቱ ቢቀርብም ኮሚሽኑ የተጠየቁት ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል እምነት ሲኖረው ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ምክንያቶቹን በመዘርዘር በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል ።

፭· የማመልከቻው ውድቅ መሆን የምዝገባውን ቀን ተቀባይነት አያሳጣውም ።

፵፬· ማመልከቻን ስለመቀበል ወይም ስላለመቀበል ውሣኔ

ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መወሰኑን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል ። ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ለመቀበል ከወሰነ ውሳኔውን ካሳወቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ውስጥ አመልካቹ የምዝገባና የሕትመት ክፍያ እንዲፈጸም መጠየቅ ይኖርበታል ።

፵፭· ስለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ፣ ሕትመትና ምስክር ወረቀት መሰጠት

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፬ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምዝገባና ሕትመት ክፍያ ከተፈጸመ ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ ፵፰(፪) እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ይመዘግባል ።

፪· ኮሚሽኑ ለሚመዘግበው ለእያንዳንዱ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በምዝገባ ቅደም ተከተል መሠረት ቁጥር ይሰጣል ።

፫· የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን መግለጫ ፣ እና

ሀ) የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ቁጥር ፣

ለ) የተመዘገበውን ባለቤት ስምና አድራሻ ፣

ሐ) ወኪል ካለ የወኪሉን ስምና አድራሻ ፣

43. *According and Notifying Filing Date; Examination*

1) The Commission shall accord as the filing date the date of receipt of the application, provided that, at the time of the receipt, the application contains indications allowing the identity of the applicant to be established and the required graphic representation of the Article embodying the industrial design. Article 12(2) of the proclamation shall apply mutatis mutandis.

2) The invitation to file any correction under Articles 12(2) and 51 of the proclamation and sub-Article (1) of this Article shall be in writing; it shall specify the correction or corrections required and request that these be filed within two months from the date of the said invitation, together with the payment of the prescribed fee.

3) Once the Commission accords a filing date, it shall so notify the applicant in writing; if the application is treated as if it had not been filed under Articles 12(2) and 51 of the proclamation and sub-Article (1) of this Article, the Commission shall notify the applicant in writing, specifying the reasons.

4) Where the Commission finds that the requirements set out in Article 48 (1) of the proclamation and Article 41 and 42 of these Regulations are not fulfilled, it shall invite the applicant, in writing, to file the required correction within two months from the date of the invitation, together with the payment of the prescribed fee; if the applicant does not comply with the invitation to correct a deficiency or, where, despite corrections submitted by the applicant, the Commission is of the opinion that the said conditions are not fulfilled, it shall reject the application and notify the applicant, in writing, stating the reasons.

5) Refusal of the application shall not affect its filing date which shall remain valid.

44. *Decision to grant or to Refuse Application*

The Commission shall notify the applicant, in writing, of its decision to grant or to refuse the application and, in the case of a decision to grant the application, it shall request the applicant to pay the registration and publication fee within one month from the date of the notification.

45. *Registration of Industrial Design, Publication of Reference thereto; Issuance of Certificate*

1) Subject to the payment of the registration and publication fee within the period prescribed in Article 44 of these Regulations, the Commission shall register the industrial design in accordance with Article 48 (2) of the proclamation and this Article.

2) The Commission shall allot to each industrial design it registers a number in the sequential order of registration.

3) The registration of an industrial design shall include a representation of the industrial design and shall specify:

(a) the number of the industrial design;

(b) the name and address of the registered owner;

(c) the name and address of the agent, if any;

መ) በምዝገባው ላይ ስሙ እንዳይጠቀስ ካልጠየቀ በስተቀር ኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ያመነጨው ሰው ስምና አድራሻ ፣

ሠ) የቀዳሚነት ጥያቄ ከቀረበና ጥያቄውም ተቀባይነት ካገኘ የቀዳሚ ቀኑንና የመጀመሪያው ማመልከቻ የተመዘገበበት ሀገር/ሀገሮች ወይም የመጀመሪያው ማመልከቻ ምዝገባ እንዲሸፍን የተጠየቀ/ቁ ሀገር/ሀገሮች ፣

ረ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት መያዝ ይኖርበታል ።

፬· በአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፪) (ሀ) እና አንቀጽ ፶፩ የሚከናወን የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ሕትመት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል ።

፭· የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት በቅጽ ቁጥር ፰ ተሞልቶ ይሰጣል ።

፵፮· ስለምዝገባ እድሳት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፶(፪) መሠረት የሚፈጸም የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ እድሳት በተመዘገበው ባለቤት ወይም በወኪሉ አማካይነት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይችላል ። የዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፫ እንደ አግባቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፪· እድሳቱ ተገቢውን የእድሳቱን ክፍያ በመፈጸም በአዋጁ አንቀጽ ፶(፪) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ወይም ከተጨማሪ ክፍያ ጋር በአዋጁ አንቀጽ ፲፯(፩) እና በአንቀጽ ፶፪ በተፈቀደው የችሮታ ጊዜ ሊፈጸም ይችላል ።

፫· የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ እድሳት በመዝገቡ ላይ መስፈርና መታተም አለበት ፣

፬· ኮሚሽኑ ለተመዘገበው ባለቤት ፣

ሀ) የአንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ ቁጥር ፣

ለ) የእድሳት ቀንና የጥበቃ ዘመኑ የሚያበቃበትን ቀን፣

ሐ) የተመዘገበውን ባለቤት ስምና አድራሻ ፣ እና

መ) ኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የተመዘገቡትን የምርት ዓይነቶች ጥቆማ የያዘ የእድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል ።

ምዕራፍ ፭
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፯· ስለባለቤትነት ለውጥ

፩· ማንኛውም የፓተንት ፣ የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀት ወይም የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ለዚሁ የቀረበ ማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል ። በተጨማሪም ማንኛውም በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ያለው ወገን ለኮሚሽኑ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ለውጡ መመዝገብና ከማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ በስተቀር በኮሚሽኑ መታተም አለበት ። የሚደረገው ለውጥ ከመመዝገቡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ የመብት ባለቤትነት ለውጥ ወይም ለዚሁ የቀረበ ማመልከቻ ባለቤትነት ለውጥ ጥያቄ በቅጽ ቁጥር ፱ ተሞልቶ የተመደበው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት ።

(d) the name and address of the creator, except where he has asked not to be named in the registration;

(e) if priority has been claimed, and the claim has been accepted, the priority date and the country or countries in which or for which the earlier application was filed; and

(f) the kind of products for which the industrial design is to be used.

4) The publication of the reference to the registration of an industrial design under Articles 14(2) (a) and 51 of the proclamation, shall contain the particulars specified in sub-Article (3) of this Article.

5) The certificate of registration of an industrial design shall be issued on Form No 8.

46. *Renewal of Registration*

1) The renewal of the registration of an industrial design may be made by the registered owner or his agent during the period referred to in Article 50(2) of the proclamation. Article 33 of these Regulations shall apply mutatis mutandis.

2) The renewal shall be made by payment of the renewal fee within the period specified in Article 50(2) of the proclamation or, upon payment of the prescribed surcharge, within the grace period allowed under Articles 17(1) and 52 of the proclamation.

3) The renewal of an industrial design registration shall be recorded in the register and shall be published.

4) The Commission shall issue to the registered owner a certificate of renewal which shall contain:

(a) the registration number of the industrial design;

(b) the date of renewal and the date of expiry;

(c) the name and address of the registered owner; and

(d) an indication of the kind of products for which the industrial design has been registered.

CHAPTER FIVE
Miscellaneous Provisions

47. *Changes in Ownership*

1) Any change in the ownership of a patent, a utility model certificate or a certificate of registration of an industrial design or in the ownership of an application therefor, shall be in writing and shall, at the request of any interested party, to the Commission, be recorded and , except in the case of an application, be published by the Commission. Such change shall have no effect against third parties until such recording is effected.

2) The request, under sub-Article (1) hereof, for the recording of a change of ownership of a title granted under the proclamation or of an application thereof shall be made to the Commission on Form No 9 and shall be subject to payment of the prescribed fee.

፫. የባለቤትነት ለውጥ ሕትመት፡

ሀ) አግባብነት ያለውን የጥበቃ ዓይነት ፣

ለ) የምዝገባ ቀን ፣ በኖረ ጊዜ ቀዳሚ ቀን እና የምዝገባ ወይም መብት የተሰጠበትን ቀን ፤

ሐ) ባለቤቱንና አዲሱን ባለቤት ፣ እና

መ) የባለቤትነት ለውጥ ፣ ባህርይን ፣ መግለጽ ይኖር በታል ።

፵፰. ስለወኪል መሰየምና የግንኙነት አድራሻ

የወኪል ስያሜ በአመልካቹ ወይም ከአንድ በላይ አመል ካቾች ካሉ በእያንዳንዱ አመልካች በተፈረመ ሀጋዊ የውክልና ሰነድ መሆን አለበት ። ከአዋጁ ወይም ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወኪል ከሰየመው ሰው/ሰዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት በወኪሉ አድራሻ ይሆናል ።

፵፱. ስለ ማይቆጠሩ ቀናት

ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን ወይም ሁኔታዎችን ለመፈጸም የተሰጠው የመጨረሻ ቀን የሚውለው የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ለሥራ ለሕዝብ ክፍት በማይሆንበት ቀን ከሆነ ተግባሩን ወይም ሁኔታውን የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ክፍት በሚሆንበት በቀጣዩ ቀን መፈጸም ሕጋዊነት ይኖረዋል ።

፶. ስለመዝገቦችና አፊሴላዊ ጋዜጣ

፩. ኮሚሽኑ ለፓተንት ፣ ለግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና ለኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የተለያዩ መዝገቦች ይኖሩታል ። በአዋጁና በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱት ምዝገባዎች በሙሉ በነዚሁ መዝገቦች ላይ ይፈጸማሉ ።

፪. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የተገለጹ ሕትመቶችን ኮሚሽኑ በአፊሴላዊ ጋዜጣ ላይ ያወጣል ።

፶፩. መዝገቦችን ስለማየት ፣ ከመዝገቦቹ የተመረጡ ክፍሎች እና የሰነዶች ቅጂዎችን ስለመጠየቅ

፩. ማንኛውም ሰው የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም መዝገ ቦችን ማየትና ከመዝገቦቹም ላይ ቅጂዎችን መውሰድ ይችላል ።

፪. ከመዝገቦች ላይ የሚወሰዱ የተመረጡ ክፍሎችን ፣ የተረጋገጡ ቅጂዎች ወይም የሰነዶችን ቅጂዎች የማግኘት ጥያቄ በጽሁፍ ሆኖ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት ።

፶፪. ስለግድፈቶች እርማት

፩. ኮሚሽኑ በቀረበለት ማመልከቻ ወይም ሰነድ ወይም በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት በተፈጸሙ ምዝገባዎች ላይ ያለን ማንኛውንም የትርጉም ግድፈት ፣ የአጻጻፍ ግድፈት ወይም ስህተት ሊያርም ይችላል ።

፪. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያከናውነው የግድፈቶች እርማት በጽሑፍ በሚቀር ብለት ጥያቄ መሰረት ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊፈጸም ይችላል ። ኮሚሽኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብ ላላቸው ሰዎች እርማቶችን በጽሑፍ ማሳወቅ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማተም አለበት ።

፶፫. ስለጉዳይ ማሰማት

፩. ኮሚሽኑ በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተሰጠውን ሥልጣን የማንኛውንም ሰው ጥቅም በሚነካ ጉዳይ ላይ ከመጠቀሙና ከመወሰኑ አስቀድሞ ለሚመለከተው ሰው ጉዳዩን ለማሰማት ዕድል እንዳለው በመግለጽ ጉዳዩን የማሰማት ጥያቄ ማቅረብ የሚችልበት ከአንድ ወር ያላነሰ የጊዜ ገደብ ሰጥቶ በጽሑፍ ያሳውቃል ።

3) The publication of the change of ownership shall specify;

(a) the title of protection concerned;

(b) the filing date, the priority date, if any , and the date of registration or grant;

(c) the owner and the new owner; and

(d) the nature of the change of ownership.

48. *Appointment of Agent, Address for Service*

The appointment of an agent shall be by a power of attorney which shall be signed by the applicant or, if there are more than one, by each applicant. The address of the agent shall, for all purposes connected with the proclamation and these regulations be used to communicate to the person or persons who appointed the agent.

49. *Excluded Days*

When the last day for doing any act of taking any proceeding falls on a day when the office of the Commission is not open to the public for business, it shall be lawful to do the act or to take the proceeding on the day when the office of the Commission is next open for business.

50. *Registers and Official Gazetta*

1) The Commission shall maintain separate registers for patents, utility model certificates and certificates of registration of industrial designs. All the recording provided for in the proclamation and these regulations shall be effected in the said registers.

2) The Commission shall publish in the official gazette all the publications provided for in the proclamation and these regulations.

51. *Consultation of Registers; Request for Extracts therefrom and for Copies of Documents*

1) Subject to payment of the prescribed fee, any person may consult the registers and may obtain extracts therefrom.

2) Requests for certified copies of extracts from a register or for copies of documents shall be made to the Commission in writing.

52. *Correction of Errors*

1) The Commission may correct any error of translation, clerical error or mistake in any application or document filed with it or in any recording effected pursuant to the proclamation or these regulations.

2) Corrections of errors under sub-Article (1) of this Article may be made by the Commission upon receipt of a request in writing or its own initiative. Corrections made shall be communicated in writing to all interested persons, and, where considered necessary, shall be published by the Commission.

53. *Hearing*

1) Before exercising adversely to any person any discretionary power given to the Commission by the proclamation or these regulations, the Commission shall notify such person, in writing, of the opportunity to be heard thereon, and indicating a time limit which shall not be less than one month, for filing a request for a hearing.

፪. ጉዳይን የማሰማት ጥያቄ የሚቀርበው በጽሑፍ ይሆናል።

፫. ኮሚሽኑ ጥያቄው ሲደርሰው ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀንና ሰዓት ለአመልካቹና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር አግባብ ላላቸው ሰዎች ቢያንስ ሁለት ሳምንት አስቀድሞ በጽሑፍ ያሳውቃል ።

፶፬. በፖስታ መልዕክት የሚደረግ ግንኙነት

፩. ማንኛውም በፖስታ አማካኝነት ለኮሚሽኑ የሚላክ ማስታወቂያ ፣ ማመልከቻ ወይም ሌላ ሰነድ ለኮሚሽኑ እንደተሰጠ ወይም እንደቀረበ የሚቆጠረው በተለ መደው የፖስታ ሥርጭት ሂደት መሰረት ለኮሚሽኑ ሲደርስ ነው ። መልዕክቱ ለመላኩ ማረጋገጫ ማስታወቂያ ው ን ፣ ማመልከቻውን ወይም ሌላ ሰነድ የያዘውን ደብዳቤ በትክክለኛው አድራሻና በአደራ መላኩን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነው ።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የምዝገባ ቀን መስጠትን አስመልክቶ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፶፭. ቅጾች

ከዚህ ደንብ ጋር በአባሪነት የተያያዙት ቅጾች ለተዘጋጁ ባቸው የተለያዩ ጉዳዮች መዋል ያለባቸው ሆኖ ኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ ለሌሎች ጉዳዮች እንዲውሉ ሊሻሻሉ ይችላሉ ።

፶፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2) The request for a hearing shall be in writing.

